# የእግዚአብሔር መንፈስ፤ የእኛ ሐይል

ክፍል አንድ

በጃኪይ ኦሴች

## ከሐዋያት ስራ መጽሐፍ የተወሰዱ ታሪኮች

ትምህርት 1፡ ንስሃ ግቡና ተጠመቁ- ጴንጤቆስጤ
ትምህርት 2፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም  - አንካሰው ሰው
ትምህርት 3፡ ሌላ ስም የለም-- ያልተማሩ ተራ ሰዎች፣ ከኢየሱስ ጋር
ትምህርት 4፡ ሂድ፤ ቁም፤ ተናገር - የተበረታታ መታዘዝ
ትምህርት 5፡ በእምነት የተሞላ ሰው - ሰማዕቱ እስጢፋኖስ
ትምህርት 6፡ ሂድ! ፊልጶስ፣ ጃንደረባው እና ሳኦል

"… አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ …"
መዝሙር 119:11

በቴንዝፓምር ፐብሊሽንግ የተዘጋጀ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው ©2015 በክሮስኮኔክት ሚኒስትሪ

ይህንን ጥናት ያለ አዘጋጁ የፅሁፍ ፈቃድ ማንኛውንም ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማባዛት ሆነ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

በጥናቱ ውስጥ የጠቀሱት ጥቅሶች የተወሰዱት ከ1962 ዓ. ም. እትም የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው፡፡

## መቅድም

ህይወታችሁን ሙሉ በሙሉ ሊቀይር ወደሚችል የትምህርት ማዕበል ውስጥ ነው የገባችሁት። ይህም የትምህርት ጊዜአችሁ በጣም በተለየ ሁኔታ፤ በትዕግስት፤ በጥሞና እና በፍላጎት መጽሐፍ ቅዱስን በጠለቀ ሁኔታ በመረዳት የምታድጉበት ነው። ይህንንም ለማጥናት የምትገቡት ቃል፤ የምትከፍሉት መስዕዋትነትና ቆራጥነት ህይወታችሁን መሉ ያደርገዋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚናገረው በቃሉ በኩል ስለሆነ ነው። በዚህ የመማርያ ጽሑፍ ውስጥ *የእግዚአብሔር ፍቅር እና የእኛን ህይወት* በሁለት ክፍሎች ውስጥ እመለከታለን።

ይህንንም ጥናት በምታጠኑበት ወቅት የሚያግዙአችሁን አንዳንድ አስፈላጊ ግብአቶችን በእጃችሁ ታገኛላችሁ።

1. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል፡ *የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የእኛ ሀይል* ፡ ክፍል አንድ
2. የምትጠቀሙት መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ የምትገዙ ከሆነ፡ እዚህ ከታች የተዘረዘሩትን ነገሮች እንዳለው ተመልከቱ
   - ሀ) የጎንዮሽ የማብራርያ ያለው መሆን አለበት። ቢቻል በገፁ መሀል ለመሀል ቢወርድ ይመረጣል።
   - ለ) በመፅሀፉ ጀርባ ላይ ሚገኝ ማጥኛ ያለው
   - ሐ) መሰረታዊ የሆኑ ካርታዎች ያሉት፤ አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙት በመጽሐፍ ቅዱሱ ጀርባ ላይ ነው።
3. እስክቢርቶ ወይም እርሳስ፤ የማስታወሻ ደብተር እንዲሁም የተቆራረጡ የማውጫ ካርድ

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሶስቱ ጥናታችሁን በአግባቡ እንድታጠኑ ያግዟችኋል። ከእነዚህ በተጨማሪ ይህንን የጥናት ትምህርት በስኬት ለማጠናቀቅ እጅግ መዘጋጀት ይጠበቅባችኋል። ነገር ግን ይህ ጥናት ለመጀመርያ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የምትገናኙበት ከሆነ ፤ *የመጽሕፍ ቅዱስ ዳሰሳ* ከሚለው ትምህርት ብትጀምሩ የተሻለ ነው። ይህም ዳሰሳ እንዴት መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት እንዳለባችሁ የሚያስችል ክህሎት እና በራስ መተማመንንም እንድታዳብሩ ይጠቅማችኋል። ምንም እንኳን *የመጽሕፍ ቅዱስ ዳሰሳ* የሚለው ጥናት እጅግ ወሳኝ እና አስፈላጊ ቢሆንም፤ አሁን ለምጠናው *የእግዚአብሔር መንፈስ እና የእኛ ሃይል* ለሚለው በጣም አስፈላጊ አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክትን ለማድረግ አታመንቱ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳችሁ እንድታጠኑት ስለሚገባ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ማስታወሻ በመያዝ፤ በማቅለም፤ የተለያዩ አይነት ምልክቶችን እንደ ቀስት፤ መስመርን በማስመር ወዘተ። በማድረግ የራሳችሁ መማርያና ማጥኛ

ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ ከፈለጋችሁም ማስታወሻ ደብተር በመጠቀም ሃሳባችሁን፣ ጥያቄዎቻችሁን እና ትምህርታቸሁን የሂደት ጉዞ ልትመዘግቡ ትችላላችሁ፡፡

የጥናቱ መማርያ በጽሑፍ ሲሆን፣ ይህም የሆነበት ምክንያት በራሳችሁ ማጥናት እና መማር እንድትችሉ ነው፡፡ እራሳችሁን በስነምግባር ከያዛችሁ፣ ያለምንም እንከን እና ችግር ጥናቱን በስኬት ልትፈጽሙት ትችላላችሁ፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ፣ የአዳዲስ መረጃ ባለቤት ትሆናላችሁ፣ ብሎም አዳዲስ አመለካከት እና አስተሳሰቦችን ለማዳበር ያስችላችኋል፡፡ ከዚያም በተረፈ የተለያዩ ከባድ የሆኑ ጥያቄዎችን እንድታነሱ እና መልሶቻቸውን እንድትፈልጉ ይረዳችኋል፡፡

እነሆ በጥናታችሁ ጊዜ ሁሉ ደስታ/ሀሴት ያግኛችሁ፡፡ እነሆ ልባችሁም እግዚአብሔር በቃሉ በሚናገርበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል የሚቀበል ይሁን፡፡ እነሆ፣ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እግዚአብሔር በልጁ በጌታችን እና በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የገለጠውን ፍቅር በይበልጥ የሚያረጋግጥላችሁ ይሁን፡፡

## መግቢያ

ከዚህ በፊት የነበረው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት *የእግዚአብሔር ፍቅር የእኛ ሃይል* በሚል ርዕስ ሲሆን ፤ ሃሳቡን ያጠቃለልነውም በማቴዎስ 28፡ 18-20 ላይ ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸውን ታላቁን ተልዕኮ በመጥቀስ ነው። ኢየሱስም አለ፤ *"ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"* የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ የመጀመርያዎቹን ክርስትያኖች ታሪክ በሚመዘግብበት ጊዜ፤ የመጀመርያዋ ቤተ ክርስትያን ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ለሰዎች ወንጌልን በመስበክ የአመኑትን ሰዎች በማጥመቅ ከዚያም በማስተማር የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ማድረግ ዋንኛ ስራዋ ነበር። እነርሱ ይህንን ሁሉ ያደረጉት ጌታቸው የሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈፀም ነበረ። የሐዋርያት ስራ መፅሐፍን እና የሉቃስን ወንጌል የጻፈው ሉቃስ ነው። የሐዋሪያት ስራ መፅሐፍ ሉቃስ ለቴዎፍሎስ የጻፈው ሁለተኛው መጽሐፉ ሲሆን፤ በእርግጠኝነት የተማረውን እውቀት ተገንዝቦ ነበር (ሉቃ 1:4)። ሀኪሙ ሉቃስ ለቴዎፍሎስ በድጋሚ ፅፎለት ነበር። ይህም ሉቃስ ለቴዎፍሎስ የነገረው የተደረገው ነገር ሁሉ ተደረገው በብዙ ሰዎች ህይወት ውስጥ ማለት ኢየሱስን በሚከተሉት ውስጥ በመስራት ላይ ባለው በእግዚአብሔር መንፈስ፤ በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፤ የመጀመሪያው እግዚአብሔር ስራ ሰማይና ምድርን እና ሁሉንም ነገር መፍጠር ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው ስራ ደግሞ የሰውን ልጆች ከሃጥያት ባርነት፤ ከሞት እና ከሰይጣን ተፅዕኖ በመስቀል ላይ በሰራው ስራ ነፃ ማውጣት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ፤መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የመጀመርያው ስራ ልባችን እና አእምሮአችንን መክፈት ነው። ይህም ደግሞ በጌታ እንድናምን እና በእምነትም የእግዚአብሔር ቃል እንዲገለጥልን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእኛ ጋር ለመኖር እና በዚያው አንድ መንፈስ ሊያነፃንና እራሱን እንድንመስል ሊያደርገን ነው። ይህንንም ስራ መቀደስ እንለዋለን። እርሱ ይቀድሰናል፤ በእግዚአብሔርም ፊት ቅዱስ ያደርገናል። በውስጣችን ውስጥ ያለው ይህ መንፈስ ብዙ ፍሬዎችን እንድናፈራ እና ያለ እርሱም ምንም ማድረግ እንደማንችል ያሳውቀናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በላከው ደብዳቤ እንደምናየው የመንፈስ ፍሬዎች እነርሱም፤ ፍቅር፤ ደስታ፤ ሰላም እና ትዕግስት በእኛ ውስጥ ይኖራሉ። እንደገናም መልካም፤

እራሳችንን የምንገዛ፣ ርህሩህ እና እርስ በእርሳችን እውነትን የምንነጋገር እንድንሆን ያስችለናል (ገላትያ 5:22-23)።

ስለ መጀመርያዋ ቤተክርስቲያን ማጥናት እንደጀመራችሁ፣ እስኪ በአትኩሮት የኢየሱስን ስቃይ እና የቤተ ክርስትያንን ስደት ተመልከቱ ። ለቤተ ክርስቲያን ከባባድ ነገሮች እና ስቃይ የማይቀር እና የሚጠበቅ ነገር ነው። ኢየሱስ እና ተከታዮቹም ያልቀረላቸው እና የጠበቁት ነገር ይህንን ነው። እንዴት ደቀ መዛሙርቱን እንዳሰሯቸው፣ በሐሰት እንደከሰሷቸው፣ እንዳገላቷቸው እና ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ስፍራ ልክ ኢየሱስን እንደወሰዱት ነበር የወሰዷቸው። ማንም ኢየሱስ ላይ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው እንደማያውቁት ሁሉ ደቀ መዛሙርቱም ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም ነበር። እግዚአብሔር እንዴት ህዝቡን እንደጠበቀ እና ከእስር ቤት እንዴት ነጻ እንዳወጣቸው፣ ከሞት ወይንም ከመገደል ነው ነጻ እንዳወጣቸው አስታውሱ። እግዚአብሔር ህዝቡን ሲናገር፣ ነጻ ሲያወጣ እና በራዕይ ሲገለጥላቸው ማየት ምንኛ ደስ ያሰኛል። አይሁድንም አሕዛብንም አንድ ላይ ይናገራል። ሁሉም እግዚአብሔር ሲናገር የሰሙት ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ ያምናሉ ወይንም የቤተ ክርስትያንን ያሳድጋሉ ያለበለዚያም ደግሞ ከመረዳ እጥረት ወደ አለማመን ይሄዳሉ።

ሉቃስ አንባቢዎቹ እንዲያውቁት የፈለገው ነገር፣ የእግዚአብሔር ማዳን ለሰው ልጆች ሁሉ መሆኑን ነው፣ እናም ይህ ማዳን ምንም ልዩነትን በሰዎች መካከል አያደርግም፣ ማንም ሰው አይሁድ ቢሆን ወይንም አህዛብ (አረማዊ)፣ ባርያ ቢሆን ጨዋ፣ ወንድ ቢሆን ሴት፣ ሁሉም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሆነዋል። እግዚአብሔር ጥሪን የሚያደርገው ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ እንዲርቡ ነው። ይህም ተልዕኮው ለሁሉም ሰዎች ነው። ለዚያም ነው ኢየሱስ *ሂዱ ዓለምን ሁሉ ደቀ መዝሙሬ አድርጓቸው ያለው*።

ቤተ ክርስቲያን ስታድግ እየተመለከታችሁ ሀሴትን አድርጉ። ትምህርታችሁንም እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማጥና ጀምሩ።

ሀ) የሐዋ2:41

______________________________________________________________________

ለ) የሐዋ 2:47

______________________________________________________________________

ሐ) የሐዋ 4:4

______________________________________________________________________

መ) የሐዋ 5:14

______________________________________________________________________

ሠ) የሐዋ 6:7

______________________________________________________________________

ረ) የሐዋ 9:31

ሰ) የሐዋ11:21

ሸ) የሐዋ 13:52

ቀ) የሐዋ 14:27

አሁን ደግሞ እግዚአብሔር በመጀመርያ እንዴት ቤተ ክርስቲያንን የለኮሰበትን እና ለህዝሁም መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሃይል የሰጠበትን መንገድ እንመልከት።

# ትምህርት አንድ

# ንስሃ ግቡና ተጠመቁ

## የሐዋርያት ስራ 1-2 ------- ጴንጤቆስጤ

---

**የትምህርት አንድ ቅኝት**

መግቢያ

ትምህርት 1፡ ሐዋርያት ስራ 1-2

- ሁሉም ሀገራት
- የበዓለ ሃምሳ ቀን
- የመንፈስ ህብረት
- የጴጥሮስ መልዕክት
- ማሰላሰል

## ትምህርት አንድ

**ክፍል 1**

***መግቢያ***

ይህ ጥናት የተሰየመው *የእግዚአብሔር ፍቅር እና የእኛ ሃይል* ተብሎ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የምንማረውም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ ዘንድ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውን ትእዛዝ እና ለአለም ሁሉ የሚሆነውን የአገልግሎት ሃላፊነትን ነው፡፡ የኢየሱስ ቃሎቹም እንዲህ የሚሉ ነበሩ፤ *አባቴ እንደላከኝ እኔም እልካችኋለሁ* (ዮሐ 20:21)፡፡" ኢየሱስ እንዲህም ብሏቸው ነበረ፤ *ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ደቀ መዛሙርቴም አድርጓቸው* (ማቴ 28:19)፡፡"

**የቤት ስራ፡** የሐዋ 1:4-8 አንብቡ፡፡

**መልመጃ**: እነዚህን ባዶ ቦታዎች ከሐዋ 1:8 ላይ የሚገኙትን ቃላቶችን በመጠቀም ሙሏቸው



1. ደቀ መዛሙርቱ የት ነው ምስክርነታቸውን የጀመሩት?

_______________________________________________

2. ከዚያስ እስከየት ድረስ ነው በስፋት የተስፋፋው?

_______________________________________________

3. ምስክርነት ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የምርጫ ጉዳይ አልነበረም፡፡

   *ሀ*. የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል በቁጥር 5: "እናንተም_______________________

   _______________________________________________"

ለ. የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል በቁጥር 8 ሀ: "እናንተም______________________

_____________________________________________________________________"

ሐ. የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል በቁጥር 8 ለ: "እናንተም______________________

_____________________________________________________________________"

4. ለምን አላማ ነበረ የመንፈስ ቅዱስን ሃይል መቀበል የነበረባቸው?

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________

ደቀመዛሙርቱ የተላኩት ወንጌልን እንዲሰብኩ እና እንዲያስተምሩ ነበረ። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ የነገራቸው ነገር ቢኖር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው እግዚአብሔር አብ የገባው ተስፋ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እስኪሰጣቸው ድረስ እንዲጠብቁ ነበረ (የሐዋ 1:4)። በዚህም ቃል መሰረት ነው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ትቶ የሄደው። ይህንም ከተናገረ በኂላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው (ሐዋ 1:9)።

**ማሰላሰል**

በዚህ ክፍል ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን መልዕክት እና ለእኛ ደግሞ ይህ መልዕክት ምን ማለት እንደሆነ በአንክሮ እንመለከታለን። በመጀመርያ በሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ታሪክ ማጥናት አስፈላጊ ነው። ከዚህም የምንገነዘበው ነገር እግዚአብሔር ይህንን ተልዕኮ ከዘመናት በፊት ነው እንደወጠነው እና እኛ ደግሞ አሁን ወደ እዚህ ታላቅ ወደ ሆነው ወደ እርሱ ተልዕኮ እንደጠራን ነው።

1. በዮሐንስ 8:31 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፤ *"እናንተ________________________________በእውነት__________________ ________________________________ናችሁ።"* ታድያ ይህ ማለት እኔ እና እናንተ ኢየሱስ በተናገረው ቃል እና ትምህርት ብናምንና ብንኖርበት ደቀ መዛሙርቱ ነን ማለት ነውን? እና እኛ ደቀ መዛሙርቱ ከሆንን ኢየሱስ አለምን ሁሉ የሚደርስበት የአገልግሎቱ ተካፋዮች ነን ማለት ነው? ለደቀመዛሙርቱ ፤ ስለዚህ ነገር ከብዙ ዘመን በፊት ወደ አባቱ ዘንድ ከመሄዱ በፊት የተናገረው ለእኛ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለምንኖር ሰዎች ይሰራል ማለት ነው?
2. በዚህ ጉዳይ ላይ የእናንተ ሃሳቦች ምንድናቸው:

_____________________________________________________________________

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**:

የአትኩሮት ማሰላሰላችንን በምንጀምርበት ጊዜ እንዲህ ብለን ጠይቀን ነበረ፤ ልክ በመጀመሪያዎቹ የጌታ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ ይሰራ እንደነበረው ዛሬም የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ውስጥ ይሰራል ፤ ነገሮችን የምናይበትን አድማስ ይሰጠናል፤ ጥንካሬን፤ ሃይልን፤ ብርታትን፤ ፀጋን ይሰጠናል። ይህም ለእኛ አስቀድሞ ያዘጋጀውን ስራ ምንፈፅምበት ነው (ኤፌሶን 2:10):: አንድ ላይ ሆነን እግዚአብሔርን የምንጠይቀውም ነገር በእምነታችንን በተስፋውን ቃል እንዲያበረታን ነው፤ምክንያቱም በማንኛውም ስፍራ እና ሁኔታ ብንሆን እንኳን እርሱ የሰጠንን ተልዕኮ ከፈፀምን እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ነው (ማቴ 28:20)።

1. ኢየሱስ እነማን ምስክሮቹ እንደሚሆኑ አስድሞነረ አቅዶ ነበረ። የእርሱ ምስክሮች ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ናቸው። ለእነርሱ ያለው እቅድ የሚጀምረውም ካሉበት ስፍራ ነበረ፤ ይህም ደግሞ ከኢየሩሳሌም ከተማ ጀምሮ ነበረ። ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሩሳሌም ወጥተው ወደ ተለያየ ስፍራ እንዲወጡ ነው ያዘዛቸው። ይህም ደግሞ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ወደ ይሁዳ ቀጥሎም እስከ ሰማርያ ከዚያም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ነበረ። ስለዚህ ኢየሱስ እኔን እና እናንተን ደቀ መዛሙርቶቼ ብሎ ከጠራን፤ የእኔ እና የእናንተ ኢየሩሳሌም ታድያ የት ነው? የእኔ እና የእናንተ ይሁዳ? የእኛ ሰማርያስ?



በዚህ ጉዳይ ላይ የእናንተ ምልከታ እና አስተያየት፡

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**<u>ክፍል 2</u>**

***መግቢያ***

ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱ በኋላ ታድያ ለምንድን ነው መንፈስ ቅዱስን እንዲጠብቁ የተነገራቸው። አንድን ነገር መጠበቅ እጅግ ደስ የሚል ልምምድ ነው። እጅግ ጥቂቶቻችን ነን ብዙውን ጊዜ መጠበቅ ደስ የሚያሰኘን። አንድን ዜና ጥሩም ይሁን መጥፎ እስኪደርሰን ድረስ መጠበቅ አስቸጋሪ ነው። በእንደዚህ ያለ ጊዜ ሰዓታችሁ መቁጠር ሁሉ ያቆመ ሊመስላችሁ ይችላል። ብዙውን ጊዜ በመጠበቅያ ስፍራ እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ላናውቅ እንችላለን። አንድ የምናውቀው እውነት ግን ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ እስኪመጣ እና ኃይልን እስኪሰጣቸው ድረስ ለአስር ቀናት ሲጠባበቁ ነበረ፤ ነገር ግን ለምን ያህል ጊዜ እንደሚጠብቁ አያውቁም ነበረ። ቀናት በአለፉ ቁጥር ሁሉ መጠበቃቸውን አላቋረጡም ነበረ። በሐዋ 1:13-14 ላይ እንደምንመለከተው ለአስር ቀናት በአንድነት ተሰብስበው፤ በላይኛው የቤቱ ክፍል ውስጥ ከሌሎች ኢየሱስን ሲከተሉ ከነበሩ ሴቶች ጋር በአንድ ላይ በመሆን ይጠብቁ ነበረ። ከደቀ መዛሙርቱ ሌላ አብሯቸው ተሰብስበው ሲጠብቁ የነበሩት ሌሎቹ ሰዎች እነማን ናቸው? ___________________________________________

_____________________________________________________________________________ክፍሉ የሚናገረው እነዚህ ሰዎች ምን እያደረጉ ይጠብቁ እደነበረ ነው? እንዴትስ ባለ ሁኔታ ነው ሲጠብቁ የነበሩት? _______________________________________________________

_________________________________________________________________________________

____________________________________________________________________

**የቤት ስራ**: የሐዋ 2:1-13 አንብቡ።

***መልመጃ***:

1. እለቱ የምን ቀን ነበረ (ቁጥር 1)?

   ___________________________________________________________________________

2. አንድ ያልተነገረን ነገር ሁሉም ሰዎች የት እንደነበሩ ነው፤ ነገር ግን ምን በእለቱ ምን እንደተከሰተ ግን ተነግሮናል:: በቁጥር 2 ላይ ስለነበረው ድምጽ የተፃፈው ነገር ምንድን ነው?

   ___________________________________________________________________________

3. በቁጥር 3 ላይ የተነገረው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ምን ይመስሉ ነበር?

   ___________________________________________________________________________

   ___________________________________________________________________________

4. እናም “በሁሉም ______________________________ሞላባቸው፤ ___________________ ይናገሩ ዘንድ ____________________ በሌላ _____________________________ጀመር፡፡” (ቁጥር 4)

5. ምክንያቱም እለቱ የበዓለ ሃምሳ ቀን ስለነበረ እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁዶች ሁሉ ከእያንዳዱ የአለም ክፍላተ አገራት በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ነበረ (ቁጥር 5)፡፡ በዚያ የተሰበሰበው ህዝብ ምላሽ ምን ነበረ?

_______________________________________________________________________________

6. ሰዎቹን ግራ እንዲጋቡ ያደረገው ነገር ምን ነበረ (ቁጥር 6 ለ)?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

7. ይህንንም ያልተለመደ ነገር ያሰኘው ነገር ምን ነበረ (ቁጥር 7-8)?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

8. እጅግ የሚያስገርመው ነገር የሐዋርያ ስራ መፅሐፍ ፀሃፊ የሆነው ሉቃስ እንዴት በጥንቃቄ እና በሚገርም ሁኔታ ከተለያዩ ሀገራ የመጡትን ሰዎች በግልፅ እንዳስቀመጠ ነው (ቁጥር 9-11)፡፡

ሀ.______________________________

ለ. ______________________________

ሐ.______________________________

መ.______________________________

ሠ.______________________________

ረ.______________________________

ሰ.______________________________

ሸ.______________________________

ቀ.______________________________

በ.______________________________

ተ.______________________________

ቸ.______________________________

አ.______________________________

ወ.______________________________

ቀ.______________________________

9. ምንም አይነት የቋንቋ ልዩነት እነዚህን ህዝቦች ሐዋርያቱ የሚናገሩትን ነገር ከመስማት አላገዳቸውም ነበረ

10. ______________________________________________________(ቁጥር11)

**አስተውሎ**

ምን ያህል ጊዜ በዚህ ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ "በራሳችን ቋንቋ" ወይም "በልሳኖቻችን" ሚለው ሀረግ ስንት ጊዜ እንደተደጋገመ ተመልከቱ፡፡ "የሚሉትን አጡ" "ተገረሙ"፤ "ተደነቁ" እንደዚህ የሚሉ ቃላቶች የሚያስተላልፉልን መልዕክት ወደ እስራኤል የመጡት ጎብኝዎች የሰሙትን ነገር በራሳቸው ቋንቋ ስለሰሙ የተነገረውን የእግዚአብሔር ቃል አድምጠው ተደንቀው እንደነበረ ነው፡፡ እርስ በርሳቸው ምን እየተባባሉ የተጠያየቁ ይመስላችኋል (ቁጥር12)?

______________________________________________________

______________________________________________________

11. በእርግጥ በዚያን ጊዜ የሚያሾፉባቸውም ሆነ የሚሳለቁባቸው ሰዎች ነበሩ (ቁጥር13)፡፡ እነዚህ ሰዎች ምን እያሉ ነበረ አስተያየት ሲሰጡ የነበሩት ?

______________________________________________________

______________________________________________________

**ክፍል 3**

**አስተምህሮ**

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደምንመለከተው የበዓለ ሃምሳ ቀን የተመሰረተው በእግዚአብሔር እንደሆነ ነው፡፡ ከፋሲካ በኋላ ለሃምሳ ቀናት የሚቆይ ክብረ በዓል ነው፡፡ ይህም በዓል እና ዝግጅት የሚከናወነው የመጀመሪያውን ምርታቸውን ለእግዚአብሔር በሚሰጡበት ሁኔታ ነው፡፡ በአንዳንድ ቤተ ክርስትያኖች በዓለ ሃምሳ ቀን ዊትሰንደይ ተብሎ ይታሰባል፤ ይህም የፋሲካ በአል ካለፈ በ50ኛው ቀን ላይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህንን የበዓል ቀን የመሰረተው፤ የእስራኤል ህዝብ ከግብፅ በወጣበት ጊዜ እና ለሙሴ ህጉን በሰጠበት ወቅት ነው፡፡ አንዳንዶች በሐዋርያት መጽሐፍ ላይ የሚገኘው የበዓለ ሃምሳ ቀን ልውጥን ያካሄደው የአይሁዶች በዓል አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ለክርስቲያን ቤተ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ውልደት/ የገና በዓል፤ የትንሳዔ/ የፋሲካ በዓል እና የበዓለ ሃምሳ ቀን ሶስቱ ታላላቅ በየአመቱ የሚከበሩ በዓላት ናቸው፡፡

ከዚህ የተማርነው ነገር ቢኖር በበዓለ ሃምሳ ቀን በአንድ ላይ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበረ እናም መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ በመገኘቱ መንፈስ እንዳናገራቸው መጠን በልዩልዩ የልሳን ቋንቋዎች ይናገሩ ነበረ (ቁጥር 4)፡፡ ንግግራቸውም ከተለያዩ ሀገራት የበዓለ ሃምሳ ቀንን ለማክበር በመጡ ሰዎች ዘንድ ይደመጥ ነበረ፡፡ እነዚህ ጎብኝዎች የሚናገሩት ልሳን ምን እንደሚናገሩ ይረዱዋቸው እና በሰሙትም ቃል እነዚያ ሰዎች በራሳቸው ቋንቋ የእግዚአብሔርን ቃል

ሲናገሩ በሰሙ ጊዜ ይደነቁ ነበረ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ አንድነትን ያመጣል፡፡ በሮሜ (15:5-6) ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡ "በአንድ____________________ሆናችሁ____________________ አፍ ____________________፥ እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፥ ታከብሩ ዘንድ፥ የትዕግሥትና ____________________አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ____________________ እርስ በርሳችሁ በአንድ____________________መሆንን ይስጣችሁ፡፡"

ማኛውም እኛን እና ማለትም የሰው ልጆችን እና የእግዚአብሔርን ግንኙነት የሰበረ ነገር ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት እና ትንሳዔ አማካኝነት ተደምስሷል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞት እና በኃጢአት እና በሰይጣን ላይ የአሸናፊነት ድልን አውጇል፡፡ ሰይጣን በአለ በሌለ አቅሙ ያደረገው ነገር የእግዚአብሔርን እና የሰው ልጆችን መለያየት እና አለመግባባትን መፍጠር ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን የቋንቋ አለመግባባት የሰው ልጆች ራሳቸውን እንዳያጠፉ በማድረግ ተጠቀመቀበት፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ በአለም ዙሪያ ተበታትነው ይኖሩ ነበረ፡፡ ይህንንም ታሪክ በዘፍጥረት 11:1-9 ላይ ተመልሳችሁ ማስታወስ ትችላላሁ፡፡

## መግቢያ

እስኪ ወደ ሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 2 ታሪክ ልመልሳችሁ፡፡ ለየት ባለው የድምፅ ምልክት እና የታዩአቸው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳናች በእያንዳዳቸው ላይ በመውረድ እና በመንፈስ በመሞላት ህዝቡ በተለያየ ቋንቋ መናገር ጀመሩ፡፡ በዚህም በታየው አስደናቂ የመንፈስ ቅዱስ ሀይል መገለጥ ምክንያት በተከሰተው ድንቅ እና የተለየ ነገር ከመደነቅ በቀር ሌላ ምንም ነገር ማለት አይቻልም ነበረ፡፡ እነኚህ ሰዎችም ከሳምንታት በፊት በር ዘግተው ተደብቀው ተቀምጠው የነበሩ ቢሆንም ከተገለጠው ሃይል እና ክብር የተነሳ በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት ለፊት በድፍረት መናገርን ጀመሩ፡፡ ቀጥሎም እንደምናየው ለእስር፤ በድንጋይ ለመወገር፤ ለሞትም ጭምር የተሰጡ ሆኑ፤ ይህም የሆነው ለጌታ እንደታዘዙት ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ለማድረስ ነበረ፡፡ እጅግ የሚያስገርመው ነገር እግዚአብሔር እንዴት ድፍረትን እና ጽናትን ለሰዎች፤ ለህዝቡ፤ እኔ እና እናንተንም ጨምሮ እንደሚሰጥ ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ሀይልን ያገኙት በራሳቸው ብቃት ሳይሆን በእግዚአብሔር ሐይል ነበረ፡፡ ምስክሮች እንዲሆኑም የተላኩት በእግዚአብሔር ሐይል በመሞላት ነው፡፡ እስኪ አሁን በአጭሩ፤ ጴጥሮስ እንዴት ለህዝቡ መልዕክት ሲያስተላፍ እንደነበረ በአትኩሮት እንመልከት፡፡

## መልመጃ

1. የጴጥሮስ መልዕክት የሚጀምረው እነዚያ ሰዎች የሰጡትን አስተያየት ማለትም "ሰክረው ነው" ላሉት ምላሽን በመስጠት ነበር፡፡ ከቁጥር 14-21 ያለውን አንብቡ፡፡

   ሀ. ለምንድን ነው በጴጥሮስ አመለካት ሰዎቹ ሰክረው ያልነበሩት (ቁጥር 14-15)?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

ለ. ነብዩ ኢዩኤል በመንፈስ ስለመሞላት በተለየ ሁኔታ ምን ብሎ ተናግሮ ነበረ (ቁጥር17)?

______________________________________________

ሐ. የእግዚአብሔር መንፈስ እንዴት ነው የተገለጠው (ቁጥር 17 ለ)?

______________________________________________

መ. እግዚአብሔር ከመንፈሴ አፈስሳለሁ ያለው በሁለቱም በምን እና በምን ነው ____________ እና________________አገልጋዮቼ (ቁጥር 18)።

ሠ. የምላሹ ባህርይ ምን የመስል ነበር (ቁጥር 19-20)?

______________________________________________

______________________________________________

ረ. ነገር ግን ከሁሉ በላይ የእግዚአብሔር መንፈስ የገለጠው ተስፋ ምንድን ነው (ቁጥ 21)?

______________________________________________

______________________________________________

2. የጴጥሮስ መልዕክት ታሪካዊ እውነታዎችን እየዘረዘር ቀጥሏል፤ ይህም ኢየሱስ ላይ የተደረገውን ያጠቃልላል ማለትም እንዴት እግዚአብሔር ለሃጥያተኞች አሳልፎ እንደሰጠው ይናገራል። ይህም የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን የመዳን እቅዱን ለመፈፀም ነው። ከቁጥር 22-36 ያለውን እስኪ ገረፍ ገረፍ እያረጋችሁ አንብቡ ከዚያም ጴጥሮስ የተናገራቸውን አንዳንድ ዋና ዋና ክስተቶች ጻፉት

   ሀ.______________________________________(ቁጥር 23)

   ለ.______________________________________(ቁጥር 24)

   ሐ.______________________________________(ቁጥር 33)

   መ.______________________________________(ቁጥር 36)

3. የጴጥሮስ መልዕክት የብዙ ሰዎችን ልብ ነክቷል (ቁጥር 37)። ምን ነበር የጠየቁት?

______________________________________________

______________________________________________

4. የጴጥሮስስ ምላሽ ምን ነበረ (ቁጥር 38)?

   ሀ.______________________________________

   ለ.______________________________________

5. ጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚገኘው ተስፋ ያቀረበው ነገር ምንድን ነው (ቁጥር 38)?

ሀ.______________________________________________________________

ለ.______________________________________________________________

6. እናም በመጨረሻው ቁጥር 41 ላይ የምናነበው … “ቃሉንም_______________ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን _______________ ሺህ የሚያህል _______________ ተጨመሩ” ። ሰዎች ለእግዚአብሔር መንፈስ ምላሽን ሰጡ፤ ይህም የሆነው ጴጥሮስ በሚናገርበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ልባቸውን በመንካት ነበረ። የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው የእነዚያን ሰዎች ልብ በመንካት ለወንጌል ምላሽን እንዲሰጡ ያደረገው።

**አስተያየት**

1. መቼም ይህንን ታሪክ ካነበባችሁ በኋላ በተለያዩ ጥያቄዎች እንደምትሞሉ እሙን ነው፤ እንዲህም ብላችሁ ጠይቃችሁ ይሆናል፡-

   ሀ. በእርግጥ ይህ ሆኗል?

   ለ. ቤትን ሁሉ የሚሞላ ድምጽ ግን ምን አይነት ይሆን? ከአንድ ቤት የወጣው ልክ እንደ እሳት አደጋ መከላከያ መኪና ድምፅ ነው?

   ሐ. እንደ እሳትም የተከፋፈለ ልሳን? ህዝቡ ሲያየው ለእነርሱ እንደ እሳት የተከፋፈለ ልሳን ምን ይመስል ይሆን?

2. ታድያ ይህ ሁሉ ምንድን ነው?

   ሀ. ከዚያ ሁሉንም ነገር ለማጠቃለል፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በተለያዩ ቋንቋዎች ይናገሩ ነበረ? እነርሱ እርስ በርሳቸው የጠየቁትን ጥያቄዎች እኛም መጠየቃችን አይቀርም፤ ይህ ምንድን ነው?

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

   ለ. እንዲህም ብለን ማሰባችንም የማይቀር ነው፤ ግን ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ እስክትሞሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ተቀመጡ የተባሉትን የጠበቁት በመንፈስ መሞላት እንዲህ ነበረ?

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

   ሐ. ደቀ መዛሙርቱ የጠበቁት ነገር ምን ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

መ. እናንተ ብትሆኑ ምን ነበረ የምትጠብቁት?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ሠ. ሌሎች ጥያቄዎች አሏችሁ፡ካላችሁ ፃፏቸው

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

3. ከዚያም ጴጥሮስ በመነሳት ስብከትን ሰበከ ያም ስብከት የብዙ ሰዎችን ልብ ነክቶ ነበረ። መልዕክቱን የተቀበሉት ሰዎች ሁሉ ተጠመቁ፤ ከዚያም 3,000 ሰዎች ተጨመሩ። ይህ እጅግ ብዙ የቁጥር ነው።

   ሀ. ንሰሃ ገቡ

   ለ. ተጠመቁ

   ሐ. ይቅር ተባሉ

   መ. ከዚያም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀበሉ

4. ጴጥሮስ ያካፈላቸው በዚያ የተከናወነውን ክስተት ይህ ነበረ (ቁጥር 14-21):: ከዚያም በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሳዔ በማመን ስለሚገኘው ድነት ነበረ የነገራቸው። መልዕክቱንም ሲያጠቃልል እንዲህ ነበረ ያለው፤ ኢየሱስ ወደ ሚገዛበት መንግስተ ሰማያት ሲያርግ መንፈስ ቅዱስን ደግሞ ለእኛ ላከልን (ቁጥር 22-36)። ከዚያም ጴጥሮስ ሰዎችን ንሰሃ እንዲገቡ፤ እንዲጠመቁ ፤ ሃጥያታቸውን ይቅር እንዲባሉ እና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንዲቀበሉ ጋበዛቸው።

   **ሀ.** አምነን እና ፈቅደን ንስሃ ስንገባ ሃጥያታችን ይታጠብልናል፤ ያለ ነውርም እንሆናለን። ይህም የክርስቶስን የማዳን ስራ ወደ እኛ ያመጣዋል። ከዚያም ባዶ ነፍሳችንን በመንፈስ ቅዱስ እና በመገኘቱ ይሞላል። ከዚያም እኛን የመቀደስ ስራውን በቀጣይነት ይሰራል ይህም የእርሱን መልክ እንድንይዝ ነው።

   **ለ.** ቀጣይነት ያለው ንሰሃ መግባት እና ይቅርታን መጠየቅ መዳናችን ሁልጊዜ ያስታውሰናል ። ይህም የእግዚአብሔር ስራ ነው። እርሱ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ባፈሰሰው ደሙ ያዳነንን እና በልጁ በኩል የራሱ እንድንሆን ብቁ ያደረገን ስራው ነው።

   **ሐ.** በምንጠመቅበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ፀጋ እንቀበላለን እናም በእግዚአብሔርም መንፈስ እንታተማለን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት የጠናከራል። እኛ የእርሱ ነን እርሱም የእኛ!

   መ. የእናንተ አስተያየት ምንድነው:

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

5. እነዚያ ሰዎች ጴጥሮስ የተናገረውን መልዕክት በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እና በእግዚአብሔር ሀይል ስለተቀበሉና ስለተጠመቁ ብዙ አይግረማችሁ። ምክንያቱም የሰውን ልብ የሚቀይር እና ሰዎች በእግዚአብሔር እንዲያምኑ የሚያደርገው እና በክርስቶስ በኩል የተገኘው ድነት ወደ ሰዎች የሚመጣው በእግዚአብሔር ስራ ብቻ ነው (ቁጥር 36)። እምነትም ቢሆን የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን የሚፈጥርልን። ኤፌሶን 2፡ 8-9 ያለውን አስታውሱ። የእናንተ አስተያየት ምንድነው:

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**የማሰላሰያ ነጥብ**

በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ ሁለት ውስጥ ወሳኙ ቁጥር ፥ ቁጥር 38 ነው። እስኪ ይህንን ቁጥር በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉት እና ንስሃ፥ ጥምቀት፥ ይቅርታ፥ እና መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ቃላት ተመልከቱ። ይህንን ክፍል በምታሰላስሉበት ወቅት እነኚህን ቃላቶች በደንብ አጢኗቸው። አሁን ይህንን የእግዚአብሔርን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚሆነውን የይቅርታ ጥሪ ለሌሎች የምታጋሩበትን አጋጣሚ ተመልከቱ፥ እናም ይህ የህይወት ጥሪ በመንፈስ ቅዱስ የሚመነጭ እና የሚጎለብት ነው።

**ፀሎት**

ጊዜን በመውሰድ ጸልዩ፥ የእግዚአብሔርንም መንፈስ ጠይቁ ወደ ንስሃ ሕይወት እንዲመራችሁ እና የእርሱን ይቅርታ እና የዘላለም ህይወት ስጦታን እንድትቀበሉ ጊዜን በመውሰድ ጸልዩ።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

# ትምህርት ሁለት

# በኢየሱስ ክርስቶስ ስም

## የሐዋርያት ስራ 3 — አንካሳው ሰው

---

**የትምህርት ሁለት**

መግቢያ

ትምህርት 2: የሐዋርያት ስራ 3

- ህብረት የማድረግ ልምድ እና ድርጊት
- ብርም ወርቅም የለም
- አስተያየት፡ አንካሳው ሰው ተፈወሰ
- የጴጥሮስ መልዕክት

***መግቢያ***

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ልምምዶችን አዳብራለች። ይህም የአማኞች የህብረት ጥንካሬ እና ፅናት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት እና ለመጸለይ ትልቅ ቦታን ይሰጡ ነበር። አንድ ላይ ህብረት ማድረግ፤ ማዕድን መቁረስ እንደሚያጠነክራቸው እና እምነታቸውን እንደ አንድ ማህበረሰብ እንደሚያጎለብት ተረድተው ነበረ። እንዴት ጠንካራ ምስክሮች እንደነበሩ እና እንዴት እርስ በርሳቸው እንደሚረዳዱ እና እንደሚደጋፉ በተግባር አሳይተዋል።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ያለው ታሪክ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ እና ለማኙን አንካሳ ሰው አንድ ቀን በቤተ መቅደስ ደጃፍ ላይ የሚያደርጉትን የቃላትን ልውውጥ እንመለከታለን። እርሱ የፈለገው ነገር ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ያልነበራቸውን ነገር ነበረ፤ የፈለገውም ገንዘብን ነበረ፤ ነገር ግን የሰጡት ነገር ያላቸውን ነበረ። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ነበረ። የምትሰጡት ነገር ሳይኖራችሁ እንዲህ ሆናችሁ ታውቃላችሁ? ያላችሁ ነገር በቂ ሳይመስላችሁ ቀርቶስ ያውቃል? ለእነዚህ ሰዎች ግን የኢየሱስ ስም በቂ ነበረ የኢየሱስ ስም የነበረውንም ሀይል ተገንዝው ነበረ።

አንካሳው ሰው መቆም ሲችል የነበረበትን ሁኔታ ተመልከቱ። እዚህ ሰው ላይ የሆነውን ነገር የሚመለከቱትን ሰዎች እስኪ ተመልከቱ። ጴጥሮስ አጋጣሚ ሲያገኝ ስለሞተው እና ከሙታን ስለተነሳው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር ተመልከቱ። እንዲመለሱ፤ ንሰሃ እንዲገቡ እና ከሃጥያታቸው ተመልሰው በእግዚአብሔር መገኘት እንዲታደሱ ይጠራቸዋል።

## ትምህርት 2

### ክፍል 1

### ትምህርት

ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ምድር በኖረበት ወቅት፤ ደቀ መዛሙርቶቹን አዲስ የሆነ የህይወት ልምምድን አስተምሯቸው ነበረ። በእነርሱ ውስጥ አዲስን ባሕርይ ከቶባቸው ነበረ፤ የተለየ አይነት ለህይወት ምለሽ ማለትም ለሰውም ለነገሮችም የሚሰጡበትን መንገድ አሳይቷቸው ነበረ። ማቴዎስ 5-7 የተራራው ስብከት ይህንን መሰል የኢየሱስን ትምህርት ይዟል። በዚህ ምድር በተመላለሰበት ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ከግል ከራሱ ህይወት ከእነርሱ የሚጠበቀውን፤ እንዴት በግል እና በህብረት መኖር እንደሚገባቸው አስተምሯቸው ነበር። ለምሳሌ፤ መንፈሳዊ ልምምዶችን አስተምሯቸው ነበረ። ይህንንም ያሳያቸው እና ያስተማራቸው፤ ለብቻው ተለይቶ በመሔድ ፀጥ ወዳለ ቦታ ማረፍ፤ መጸለይን አሳይቷቸዋል። እንደገናም እንዴት ከሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር እንደሚችሉ፤ ከቀራጮች ጋር፤ ከኃጥአኞች ጋር፤ በህብረተሰቡ ዘንድ ጥሩ ስዕብና ከሌላቸው ሰዎች ጋር፤ በድብቅ ከቤተ መቅደስ መሪዎች ጋርም በመገናኘት እንዴት በመንፈስ እና በስጋ ከታወሩ እና ከተያዙ ሰዎች ጋር ግንኙነትን መፍጠር እንዳለባቸው አሳይቷቸዋል። እነኚህ ባህርያት እና ድርጊቶች ደግሞ በአይሁድ ህግና ስርዓት ውስጥ ተቀባይነት እና ስፍራ የሌላቸው ነበሩ።

ነገር ግን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ትቷቸው ሲሄድ ምን የሚያጋትማቸው ይመስላችኋል? ወደ ድሮው ልማድ እና ድርጊታቸው የሚመለሱ መስሏችኋል፤ ወደ ቀድሞው ህጋቸው ይመለሳሉን? ኢየሱስ ያደረገው ነገር ወደ ፊት የሚያስፈነጥር እና የሚያራምድን መሰረት ነው ማንነታቸው ውስጥ የከተተው። መጀመርያ እንዲህ ብሏቸው ነበረ፤ ተከተሉኝ፤ አሁን ደግሞ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት የነገራቸው ነገር ቢኖር ምስክሮቼ ትሆናላችሁ የሚል ነው። እነርሱም ኢየሱስን ተከተሉት፤ የእርሱንም መንገዱንም ሁሉ በመከተልና በመማር ለዓለም የእርሱ ነጸብራቅ ሆኑ። ስለዚህ አሁን ለተፈጠሩለት ማንነት ኖሩ ማለት ነው። ይህም የተፈጠሩበት ማንነት የእግዚአብሔር አምሳል ለመሆን ነው (ዘፍጥረት 1:27)። አሁን በመንፈስ ቅዱስ ስለተሞሉ እና ብቃትን ስላገኙ፤ ይህም ብቃት ስለክርስቶስ ምስክሮች ለመሆን ለሚሰሟቸው ሁሉ አቅምን ይሰጣቸዋል።

ከሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 2 የምንማረው ነገር እነዚህ አንዳንድ ባህሪዎች ምን እንደሚመስሉ ነው። የኢየሱስ ተከታዮች ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ከተቀበሉ በኋላ እንዴት ኖሩ?

**የቤት ስራ፡**

የሐዋ 2:42-47 አንብቡ። በምታነቡበት ወቅት እነዚህን ቃላት በጥሞና ተመልከቷቸው፤ እነርሱ፤ “እያንዳንዳቸው” እና “ሁሉም” የሚሉት ቃላት በስፋት በእዚህ ክፍል ውስጥ ተጠቅመውበታል። እነኚህ ቁጥሮች የሚገልጹት የመጀመርያዋ ቤተ ክርስቲያን አማኞች እንዴት ህብረትን እንደሚያደርጉ፤እና እንዴት በአንድነት በህብረት እንደሚኖሩ ያሳየናል። አብረው ሲኖሩ ምን አይነት ልምዶችን እና ባህርያትን አዳብረው ይሆን?

**መልመጃ**:

1. ምንድን ነው በቁጥር 42 ላይ የተመለከታችኋቸው አራት በጋራ የመኖር ልምድ ፤ ህብረት እንዲኖራቸው ያደረገው?

   ሀ.____________________________________________________________

   ለ.____________________________________________________________

   ሐ.____________________________________________________________መ.____

   __________________________________________________________

2. የህብረታቸው ምላሽ ምን ነበረ፤ መንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ተዓምራትን እና ድንቆችን በሐዋርያቱ በኩል ሲያደርግ (ቁጥር43)?

   ________________________________________________________________

3. አማኞች በህብረት ይኖሩ ነበረ። ያላቸውን በልግስና እርስ በርሳቸው ይካፈሉ ነበረ እና የተቸገረውን ለመርዳት የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጉ ነበረ (ቁጥር 44-45)። ያላቸውን ንብረት ሁሉ በፍቃዳቸው ለሌላቸው ይሰጡ ነበረ። በዚህ ቁጥር መሰረት ስለ አኗኗራቸው ምን ትረዳላችሁ?

   ______________________________________________________________________

   ____________________________________________________________

4. ቁጥር 46-47 ስለ አማኞች የአምልኮ ልምምድ ይናገራል። በመደበኛ የአምልኮ ስርዓት ውስጥ ይካፈሉ ነበረ፤ ብሎም በቤተ መቅደስም ውስጥ ያመልኩ ነበረ። እንደገናም በግል በየቤታቸው ከቤተሰቦቻውም ጋር ያመልኩ ነበረ። እንደገናም አብረው ማዕድን ይቆርሱ ነበረ ____________________እናም ________________________ ልቦች።

5. በቁጥር 47 ላይ ሚነግረን “እግዚአብሔርንም___________________ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ____________________የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ___________________ ነበር።” በህዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስን በማግኘት የማይቀረው የሚከሰት እውነታ ምን ይመስላችኋል ውጤት?

   __________________________________________________________________

6. ቁጥር 47ለ እንደሚገልጠው ውጤቱ፤ ጌታ ______________________________

____________________________________________________ይጨምር ነበር።

ወንጌል መስበክ፤ እምነትን ማካፈል፤ እለት ተእለት ልምምዳቸው ነበረ።

**ክፍል 2**

**አስተያየት፡-** የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አራት አይነት መሰረታዊ ልምምዶች ነበሯት።

1. ሕይወታቸው ማዕከል ያደረገው የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር፤ ማጥናት፤ መፀለይ እና መኖር ላይ ነው
2. የሕይወታቸው ልምምድ የተሞላው በህብረት ውስጥ ነበረ፤ የአንዱ መኖር ለሌላው ደስታ ነበረ እንደገናም ካላቸው ላይ በልግስና ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ይሰጡ ነበረ።
3. ሕወታቸው በአምልኮ የተሞላ ነበረ፤ ይህም በትልቁ ጉባኤም እናም በትንንሽ ጉባኤዎች ውስጥ የጠበቀ ነበረ።
4. ሕይወታቸው እንደሚጠበቀው እና እንደሚገመተው ያድግ ነበረ።

**ከሕይወት ጋ ማዛመድ**:

1. የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ያገኘችውን አዲስ ማንነት ማለትም የክርስቶስ ምስክርነት የተቀበለችበትን መንገድ እንዴት ትመለከቱታላችሁ፤ ምንስ ይመስላችኋል?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

2. የትኛው ልምምድ ነው እናንተን ይበልጥ የሚመስጣችሁ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

3. የትኛውስ ልምምድ ነው ምቾትን የማይሰጣችሁ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4. የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን ባህርይ እና የጋራ ግንኙነትን እንዴት ትመለከቱታላችሁ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

5. ይህንን የክርስቶስ ምስክርነት ማንነት ከተሰጣችሁ በኋላ የራሳችሁ ባህርይ ከዚህ አዲስ ማንነት ጋር ሲጣረስ ታገኙታላችሁ? ከሆነ አብራሩት ጉዳዩን አብራሩ

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

6. የእናንተ ልምምድ ወይንም ባህርይ ከጌታችን ከክርስቶስ እና እርሱ ከሚፈልጋት እውነተኛዋ ቤተ ክርስታያን ከመመሰል ጋር ለመዋሀድ ምን መደረግ አለበት ትላለችሁ (የሐዋ2:42-47)? የእግዚአብሔርን መልክ በትክክል ለመግለጥ ምን አይነት ማሻሻያ ማድረግ ይጠበቃል ትላላችሁ?

______________________________________________

______________________________________________

**ጸሎት**

ኦ እግዚአብሔር፤ በመንፈስህ አሁንም እኔን ማስተማር ቀጠልክ፡፡ እግዚአብሔር ሆይ እንድከተልህ ብቻ ሳይሆን ከአንተ ጋር የተልዕኮህ ተካፋይ አደረከኝ፡፡ አጠብከኝ፤ ከሃጥያት በልጅህ በኢየሱስ ደም አነጻኸኝ ከዚያም በተጠመቅኩኝ ጊዜ በመንፈስህ ሞላኸኝ፡፡ እውነተኛ የንተአ ምስክር እሆን ዘንድ አስችለኝ፡፡ ይቅር በለኝ፤ አበርታኝ ለአዲሱ ማንነቴ ጥሪ ታማኝ ሆኜ እንድኖር አበርታኝ ፤ ስወድቅም አንተው አንሳኝ፤ ሃይልንና ብርታትን ስጠኝ፤ ያዘኝ፤ በመንፈስህ፤ በጸጋህ እና በምህረትህ ምስክርህ ሆኜ እንድኖር ዘንድ ይርዳኝ፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**ክፍል 3**

***መግቢያ***

የኢየሱስ ተከታዮች ኢየሱስ የሚያደርገውን ይመለከቱና ከእርሱም ይማሩ ነበረ፡፡ የኢየሱስ ምስክሮች የሆኑት የኢየሱስ መገኛ ነበሩ፤ ኢየሱስ ያደረገውን ያደርጉ ስለነበረ፡፡ በማቴዎስ 28፡18 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ነበር "ስልጣን ሁሉ ተሰጥቶኛል" እናም በዚህ ስልጣን ነው ተከታዮቹን ምስክሮቹ እንዲሆኑ እና ደቀ መዛሙርትን እንዲያፈሩ ያስታጠቃቸው፡፡ በማርቆስ 16፡ 17- 18 ላይ የሚያምኑትም እነዚህን ምልክቶች ይከተሏቸዋል ብሎ ይነግረናል "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ፡፡" ሰዎችን የሚፈውስ እና አሁንም እኛን ተጠቅሞ የሚፈውሰው ኢየሱስ እንደሆነ ሁልጊዜ ማስታወስ ይገባናል፡፡ በሐዋ ስራ ምዕራፍ 3 እና 4 ላይ እንዳለው ከአንካሳው ሰው ፈውስ እንደምንማረው ማለት ነው፡፡

**የቤት *ሥራ*፡** የሐዋ፡፡ *ሥራ* 3፡ 1-10 አንብቡ

- በታሪኩ ውስጥ ያሉት ገፀ- ባህሪያት እነማን ናቸው?

- ምንድን ነው የተካሔደው?
- የህዝቡስ ምላሽ ምን ነበር?

**መልመጃ**

1. ሁለቱ ደቀመዛሙርት እነማን ነበሩ (ቁጥር 1)?

   __________________________ እና__________________________

2. የት እየሔዱ ነበር?

   ____________________________________________________________________

3. ለምን ነበር የሚሔዱት?

   ____________________________________________________________________

4. በቀኑ በስንተኛው ሰዓት ነበር?

   ______________________________________________________________

5. በቁጥር ሁለት ላይ የተለዩ ነገሮች ተነግረውናል ፡

   **ሀ**. ስለዚህ ሰው ምንድን ነው የተነገረን?

   _____________________________________________________

   **ለ.** የት ነበር የተሸከሙት?

   ______________________________________________________________

   **ሐ**. የበሩ ስም ምን ይባላል?

   _______________________________________________________

   ካርታ ቢኖራችሁ፤ በሩን አመልክታችሁ ከዚያም ከሴቶቹ መቀመጫ ጋር ያለውን ዝምድና እና የአህዛቦች መቀመጫ የሆነውን የምስራቁን የመቅደስ አቅጣጫ ታዩ ነበር። በሩ የተከፈተው ወደ ሴቶቹ መግቢያ እና ወደ ቤተ መቅደሱ ዋና መግቢያ ነው። በሮቹ እጅግ መሳጭ ሲሆኑ የተሰሩትም ከቆሮንቶስ ብረት ሲሆኑ እጅግ ግዙፎችም ነበሩ።

   **መ.** ሁልጊዜ በቤተሰቦቹ እና በጓደኞቹ አማካኝነት ወደ በሩ እንደሚመጣ መገመት ይቻላል። ለምን እዚያ ጋር የሚቀመጥ ይመስላችኋል?

   ____________________________________________________________________________

6. ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ባየ ጊዜ ምን ያደረገ ይመስላችኋል (ቁጥር 3)?

   ______________________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________________

7. የጴጥሮስ እና የዮሐንስስ ምላሽ ምን ነበረ (ቁጥር 4)?

8. ከዚያስ፤ ጴጥሮስ ለሰውዬው ምንድነው ያለው?

9. ሰውዬው ምን አደረገ (ቁጥር 5) ______
ለምን?

10. ይልቁንም ጰጥሮስ ምን እንዲያደርግ ነገረው (ቁጥር 6)?

11. ጴጥሮስ ቀኝ እጁን ይዞ እንዲነሳ ረዳው እና "______
የእርሱ______ እና______ አንድ ላይ
ሆነው______:: "

12. በቁጥር ስምንት ሀ ላይ ሰውዬው ምን አደረገ ነው የሚለው?

ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ከጴጥሮስ እና ከዮሐንስ ጋር ሊገባ የቻለው እንዴት ነው (ቁጥር 8 ለ)?

13. ሁሉም ሰዎች ባዩት ጊዜ

ሀ. ምን እያደረገ ነበረ (ቁጥር 9)?

ለ. ቁጥር 10፡ እነርሱም ______::

ሐ. እንዴት አወቁት?

መ.እናም እነርሱም

______::

**ክፍል 4**

**አስተያየት**:

1. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ለቤተ መቅደሱ እና ለሚያምረው መግቢያ/ ደጃፍ መቼም እንግዳ ሰዎች አልነበሩም ምክንያቱም ይህ ከድሮም ጀምሮ የተለመደ የመቅደሱ መግቢያ ደጃፍ ነው ፡፡ በእርግጠኝነት ከዛሬ በፊትም ይህንን አንካሳ ሰው ተመልከተውት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ወደ ቤተ መቅደሱ ደጃፍ ዘወትር ይመጡት ስለነበረ ነው፡፡ ነገር ግን ዛሬ ልዩ ነበረ፡፡ መጽሐፉ እንደሚነግረን ከሆነ አንዳች ፈልጎ ሲለምናቸው ጴጥሮስ ትኩር ብሎ ተመለከተው ፡፡ ጴጥሮስ እና ዮሐንስም እንደሌላው ቀን አልፈውት አልሔዱም ነበር፡፡ ይልቁንም ቆም አሉና መጽሐፍ እንደሚነግረን አይኑን ተመለከቱት ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ መገመት እንደሚቻለው ወዲያው ስላሰጡት ወደ ሚቀጥሉት ሰዎች ልመናውን ቀጥሎ ሊሆን ይችላል፡፡ ምን አልባትም ይህ ሰው በሁለቱ ድርጊት ትንሽ ተናድዶ ሊሆንም ይችላል ምክንያቱም ሌሎቹን ሰዎች እንዳያይ ከልለውትም ይሆናል፡፡ ነገር ግን ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ቆም ብለው አይኑን ትኩር ብለው ከተመለከቱት በኋላ ፤ ተመልከተን አሉት፤ ከዚያም ጴጥሮስ እንዲህ ያለ ይመስላል ተመልከተን ይኸው ቆምን፤ አንተ የደጃፍ ማድመቂያ ሳትሆን ሰው ነህ፤ ከዚያም ሰውዬው አትኩሮቱን ለእነርሱ የሰጠው፡፡
2. እንደተነገረን ሰውዬው ከእነርሱ አንዳች ያገኝ መስሎት ተመለከታቸው ይለናል፡፡ በሰውዬው አዕምሮ ውስጥ ምን የተፈጠ ይመስላችኋል፤ ልክ ጴጥሮስ የመጀመሪያውን ቃል ሲያወጣ እኛ ብርም ወርቅም የለንም ሲል፤ ሰውዬው እንዲህ የሚል ይመስላችኋል፤ ብርም ወርቅም ባይኖራቸውም ምንም አይደለም፤ ብቻ ዞር በሉልኝ የሚል ይመስላችኋል፡፡ ወይስ እንዲህ የሚል ይመሰስላችኋል፤ ባይኖራችሁም የስራዬ ባህሪይ ነው ሌሎች ያላቸውን እጠይቃለሁ፤ አንዳንዶች ባይሰጡኝ ሌሎች ሊሰጡኝ ስለሚችሉ መጠየቄን እቀጥላለሁ፡፡
3. ከዚያ ግን ጴጥሮስ ንግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ፤ ነገር ግን ያለንን እንሰጥሃለን፡፡ ግን ጴጥሮስ ምንድን ነው የሚሰጠው? "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሳና ተመላለስ አለው" ይህን ካለ በኋላ ጴጥሮስ ንግግሩን አልገፋበትም ይልቁንም ሰውዬው ተነስቶ እንዲም ይረዳው ጀመረ፤ ከዚያም ወዲያውኑ ሰውዬው ቁርጭምጭሚቱ ፀንተው በእግሮቹ መቆም ቻለ፡፡ ከዚያም እየዘለለ ከወዲያ ወዲህ ይሄድ ጀመረ፡፡ ጴጥሮስ ያደረገው ነገር ቢኖር ያለውን የክርስቶስን ስም መስጠት ነው ሰውዬውም የሚያስፈልገው ይህን ስም ነበረ፤ የኢየሱስን ስም፡፡በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ተሞልቶ ጴጥሮስ በኢየሱስ ስም አምኖ ሽባውን ሰውዬ እጁን በመያዝ ደግፎ እንዲቆም ረዳው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሀይል ለጴጥሮስ ተሰጥቶት ነበረ፤ ስለተጠቀመው ሰውዬውም ተፈወሰ፡፡
4. የሰውው ምላሽ ማመስገን እና ማምለክ ነበረ፡፡ ለመጀመርያም ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ መግባትን ቻለ፡፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና እየሰጠ ከጴጥሮስ እና ከዮሐንስ ጋር ሄደ፡፡ ካለሽክም

ምንም መንቀሳቀስ የማይችለው ሰው አሁን ግን የእግዚአብሔር ሃይል በህይወቱ በሰራው ስራ በጴጥሮስ እና በዮሐንስ ምስክርነት ህይወቱ የምስክርነት ሆነ።

5. ሰዎቹም በቤተመቅደስ ደጃፍ ላይ የሚለምነው ሰው መሆኑን አውቀው ነበረ። አሁን ግን እያመሰገነና እያመለከ ሲመላለስ አዩት። መጽሐፍ እንደሚነግረን በሰውዬው በሆነው ተዓምር እጅግ እንደተገረሙ ነው። እስኪ በሽባነት ታስሮ የነበረበትን ህይወቱን አስቡ፤ ምን ይከሰት እንደነበረ? የእናንተን ሃሳብ ምንድነው፡

____________________________________________________________

____________________________________________________________

*መግቢያ*

ጴጥሮስ የተሰበሰበው ህዝብ በሞላ ወደ እርሱ እና ወደ ዮሐንስ እየመጡ እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። ህዝቡም በተፈጸመው ክስተት እጅጉን ተደምመው ነበረ። ጴጥሮስም ይህንን እንደ ትልቅ አጋጣሚ በመጠቀም አንካሳውን ሰው ስለፈወሰው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መናገር ጀመረ።

**የቤት ስራ**፡ የሐዋ ሥራ 3:11-20 አንብቡ

***መልመጃ***:

1. ጴጥሮስ የጀመረው ሁለት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነበር (ቁጥር 12):
   ሀ.____________________________________________________
   ለ.____________________________________________________
2. ሰውዬው የተፈወሰው በኢየሱስ ስም ነው። ጴጥሮስ ማንን ነው ኢየሱስን ከፍ ያደርገዋል ያለው (ቁጥር13)?

   ____________________________________________________________
3. ጴጥሮስ ለሰዎቹ ምን እንዲያደረጉ ነበር የነገራቸው (ቁጥር 13 ለ-15 ሀ)?
   ሀ.____________________________________________________
   ለ.____________________________________________________
   ሐ.____________________________________________________
   መ.____________________________________________________
4. ጴጥሮስ ለህዝቡ ምን ብሎ ነው እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ የነገራቸው (ቁጥር 15 ለ)?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

   ከዚያም ጴጥሮስ እንዲህ አለ፡ ለዚህም እኛ ______________________

5. ከዚያም በቁጥር 16 ላይ ጴጥሮስ በመቀጠል ዘርዝሮ ሲናገር እንመለከታለን። "በስሙም________________________ ይህን የምታዩትንና ________________________ የእርሱ ________________________ አጸናው፥ በእርሱም በኩል የሆነው_____________________ በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ________________ ሰጠው።"

6. ጴጥሮስም በመቀጠል እንዲህ ብሎ ተናገረ "እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን እንዲሁ ፈጸመው።" ከዚያም በ19 ኛው ምዕራፍ ላይ ጴጥሮስ"____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

_____"ብሎ ጥሪን አቀረበላቸው።

7. በ25ኛው ቁጥር ላይ ደግሞ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ያስታውሳቸዋል፤ "እናንተ___________________ ልጆችና ___________________ ለአብርሃም። በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ___________________ ብሎ፥ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው ___________________ ልጆች ናችሁ።"

8. ከዚያም ጴጥሮስ ስለኢየሱስ ፤ "ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው።" (ቁጥር 26)በ ማለ ት ተናገረ።

# ትምህርት ሶስት

# ሌላ ስም የለም

## የሐዋርያት ሥራ 4 — ያልተማሩ፤ ተራ ሰዎች ፤ እና ግን ከኢየሱስ ጋራ

---

**የትምህርት ሶስት**

መግቢያ

ትምህርት 3: የሐዋርያት ስራ 4

- የጴጥሮስ እና የዮሐንስ መታሰር
- መዳን በሌላ በማም የለም
- አስተያየቶች
- ትምህርት፡ 1ኛ ቆሮንቶስ 5:12-22
- ከአይሁድ ሸንጎ/ጉባኤ በፊት
- መፈታት
- መጸለይ

## መግቢያ

የጴጥሮስ እና የዮሐንስ ትምህርት አንዳንዶቹን ባለስልጣናት አስቆጥቶ ነበረ። በዚህም ምክንያት እንዲታሰሩ አደረጓቸው። ልክ ኢየሱስን ሲያስተምር እያዩት በአድናቆት የሚሰሙት ሰዎች እንደነበሩ ሁሉ በቅናት ተነሳስተው ኢየሱስ እንዲታሰር እና እንዲሰቀልም ያረጉት የእነርሱን ትምህርት ከሚሰሙ ሰዎች መካከል አንዳዶቹ ነበሩ። በኢየሱስ ላይ የደረሰው በተከታዮቹም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ አሁን ይከሰትባቸው ይሆን? የጌታ ደቀ መዛሙርት መናገራቸውንስ ያቆሙ ይሆን? ሉቃስ እንደሚነግረን ከሆነ እነርሱ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው እንደነበረ ነው። ከዚያም በመናገር ላይ እያሉ ነው አንድ አስደናቂ ነገር ተከሰተው፤ እርሱም በኢየሱስ ስም ነው ያ አንካሳ ሰው ተነስቶ ተመላለሰ።

የጌታ ደቀ መዛሙርት እየፈሩ ነበረ እንዴ የተናገሩት? በሰሙት እና ባዩትስ ነገር አመንትተው እና ወደኋላ አፈግፍገውስ ነበር? ተሰብስበው የሚሰሟቸውስ ሰዎች ምልሽ ምን ነበር? የአይሁድ ሸንጎ አባላት ተመልክተዋቸው ምነድን ነው ያሉት? ስለ ኢየሱስ ክርሰቶስ ስም መናገርና ማስተማር እንዲያቆሙ ሲነግሯቸው ምላሻቸው ምን ነበር?

ጴጥሮስ እና ዮሐንስ አንዴ ከተፈቱ በኂላ፤ ለጓደኞቻቸው ያጋጠማቸውን ነገር ለመናገር ነበር የተመለሱት። አስቡት እስኪ ከእነርሱ ይህንን ታሪክ ሲሰሙ የሰሟቸው ሰዎች ምን ያህል የኢሱስ ምስክሮች መሆን እጅግ ግሩም ዕድል መሆኑን ይገነዘባሉ። ሁሉም ሰዎች እነርሱን የተቃወሙት መሪዎች እና ሌሎች የተነሱት በእነርሱ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ እና እግዚአብሔር በተቀባው፤ በኢየሱስ ላይ እንደተነሱ ነው።

**ትምህርት 3**

**ክፍል 1**

***መግቢያ***

ጴጥሮስ በመልዕክቱ ውስጥ ነብያት እንደ ሙሴ፤ ሳሙኤል እና የአብረሃም ያሉት ስለመሲሁ መምጣት እና እግዚአብሔር ከሞት እንደሚያስነሳው ትንቢትን ተናገረው ነበር። የጴጥሮስ ንግግር እስከዚህ ድረስ ተቋውሞ አልደረሰበትም ነበር ነገር ግን ልክ ስለ መሲሁ ከሞት መነሳ እና ማረግ ሲናገር ግን ተቃውሞው የደረሰበት። ሰዱቃውያን የእስራኤል ውስጥ በወቅቱ ከሚገኙ የሃይማኖት ክፍሎች አንዱ ሲሆኑ በሙታን ትንሳኤ አያምኑም ነበር።

**የቤት ስራ፡** የሐዋ 4፡ 1-22 አንብቡ

***መልመጃ፡***

1. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ እየተናገሩ እያለ ማን ነው የመጣው (ቁጥር 1)?

 ______________________________

2. ምንድን ነው እንደዚህ ባለ ሁኔታ ክፉኛ እንዲቆጡ ያደረጋቸው ነገር (ቁጥር 2)?

 ______________________________

 ______________________________

3. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ላይ ምን አደረጉባቸው (ቁጥር 3)?

 ______________________________

 ______________________________

4. ከመታሰራቸው ውጭ ሌላ ምን የተፈጠረ ነገር አለ (ቁጥር 4)?

 ______________________________

 ______________________________

5. በሚቀጥለው ቀን ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በማን ፊት ነው የቀረቡት (ቁጥር 5-6)?

 ______________________________

6. ______________________________

 ከእነዚህ ክሶች አንዳንዱ ከኢየሱስ ክስ ጋር ተመሳሳይት አለው ?

 ______________________________

7. እነኚህ ሰዎች ሊያውቁ የሚፈልጉት ነገር ምንድነው (ቁጥር 7)?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

8. ጴጥሮስ የተሞላው በ ______________________________ነበር (ቁጥር 8) እናም እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ ለአንካሳው ሰው ለምን ምህረት እንደተደረገ ማወቅ ከፈለጋችሁ እና እንዴት ፈውስን እንዳገኝ ለማወቅ ከጠየቃችሁ ዘንዳ ይህንን ነገር እወቁ…። ለሚከስሱት ሰዎች ምንድነው እያወጀ የነገራቸው ( ቁጥር 10)? "እናንተ በ________________ እግዚአብሔርም ከሙታን ________________ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ________________ ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፥ ለእናንተ ለሁላችሁ ________________ ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን።"

9. በቁጥር 12 ላይ ጴጥሮስ ያወጀው ነገር ፡ "መዳንም በሌላ______________________የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ______________________ የተሰጠ ስም ______________________በታች ሌላ የለምና።" በመቀጠል እየተናገረ የነበረው ነገር ምንድን ነው?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

10. የአይሁድ ሸንጎው ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ላይ ምንድነው ያየው (ቁጥር 13)?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

11. ስለእነዚህ ሁለት ሰዎች ምን ነበር ያስደመማቸው?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

12. ሌላስ ምንን ነገር ተገነዘቡ?

_______________________________________________________________

13. ከሽባነት የተፈወሰው ሰው ከጴጥሮስ እና ከዮሐንስ ጋር መሆኑን ሲመለከቱ ምን ሊሉ ይችላሉ? ከዚህ ከአይሁድ ሸንጎ እዲወጡ አደረጓቸው በኋላ ______________________________ ተባባሉ (ቁጥር 15)።

14. እነርሱን ያሳሰባቸው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 16)?

_______________________________________________________________

15. ችግሩ ምን ነበር?

ሀ.____________________________________________________________

ለ.____________________________________________________________

16. ያመጡትስ የመፍትሔስ ሃሳብ ምን ነበር (ቁጥር 17)?

17. ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ወደ ክፍል ውስጥ በመጥራት ምን ብለው ነበር ያዘዟቸው (ቁጥር 18)?

18. ለትዕዛዙስ የጴጥሮስ እና የዮሐንስ መልስ ምን ነበረ (በተለይ ቁጥር 20)?

19. ሸንጎውም ቤቱም በድጋሚ አስፈራራቸው እና ______________________ (ቁጥር 21)።

20. ያልተረዱት ነገር ምን ነበር?

21. ችግር ውስጥ የጣላቸው ነገር ምድን ነበር?

22. ስለ ተፈወሰው አንካሳ የተነገረን ምንድነው የተነገረን (ቁጥር 22)?

**የማሰላሰያ ነጥቦች**

የሐዋ 4:12 አሁን ስላለው ዘመናዊ ማህበረሰብ እጅግ ብዙ የሚናገረው ነገር አለው። ሰዎች ለመዳን ብዙ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን መንገዶች ሲመርጡ ይስተዋላል። አንዳንዶች ደግሞ በመልካም ስራ ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ በአባቶቻው አምላክ ያምሉ። የተቀሩት ደግሞ በራሳቸው መልካምነት የተነሳ እንደሚድኑ አድርገው ያስባሉ ደግሞም ያምናሉ። አንድ ሰው የመዳን መንገድ ብሎ ከሚያስበው ይልቅ፤ የሐዋርያት ስራ 4፡ 12 የሚነግረን እውነት እግዚአብሔር እንዳለው ነው "መዳንም በሌላ______________________የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ______________________ የተሰጠ ስም ______________________በታች ሌላ የለምና።" እኛ ሁላችን የዳነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው ! ይህንንም ጥቅስ በሌላ ማስታወሻ ደብተር ላይ ጻፉት። በጆርባው ላይ ያስተዋላችሁትን አዲስ እና ለየት ያለ ነገር ሰዎች ያድናል ብለው የሚያምኑት ነገር ካለ ማስታወሻ ውሰዱ። አስታውሱ፤ ድነት በኢየሱስ ክርቶስ ብቻ ነው የሚገኘው!

## ክፍል 2

**አስተያየት**:

1. ይህ አስደናቂ ታሪክ የሆነው ኢየሱስ ከተሰቀለ ከትንሽ ሳምንታት በኋላ ፤ እነዚያ ክርስቶስን የሰቀሉት የሐይማኖት መሪዎች ናቸው ጴጥሮስን እና ዮሐንስን ያሳሰሯቸው፡፡ ጴጥሮስም በልበ ሙሉነት እዚያ ለተሰበሰበው ሰው ሁሉ ሲሰብክ እነርሱም እጅግ እየተገረሙ በዚያ ከሰዓት ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ ይገቡ ነበረ፡፡ አንካሳው ሰው ተፈውሷል፡፡ መፈወስ ባቻ ሳይሆን እየተራመደ፤ ከወዲያ ወዲህ እየዘለለና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ነበረ፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስም ሰውዬውን ዝም አላሰኙትም ልቁንም ባገኙት በዚህ አጋጣሚም በድጋሚ ስለ የናዝሬቱ ኢየሱስ፤ እነርሱ አሳልፈው ስለሰጡት፤ ስላስፈረዱበት እና ስለገደሉት ነገር ግን ሞትን ድል አድርጎ ስለተነሳው ስለ ክርስቶስ መናገራቸውን ጀመሩ፡፡ ጴጥሮስ በአበክሮ ይናገር የነበረው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመኑ እና በኢየሱስ ስም ይህ ሰው ፍጹም የተፈወሰው በሆኑን አበክሮ በመግለፅ ነበር፡፡
2. ካህናቱ የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች እና ሳዱቃውያኑ፤ ጴጥሮስ እና ዮሐንስን ያሰሩት ሰዎች እስከሚመጡበት ጊዜ ድረስ ሁሉም ነገር ሰላም ይመስል ነበር (ሉቃስ 22፡ 25) ፡፡ ለምን ግን ጴጥሮስንና ዮሐንስን አሰሯቸው? ጴጥሮስ እና ዮሐንስ የእየሱስን ከሞት መነሳት ያውጁና ይናገሩ ነበር ፡፡ አስታውሱ፤ እነኚሁ ሰዎች ናቸው ኢየሱስ ከሞት ሲነሳ ደቀ መዛሙርቱ ሳይሰሙ ገንዘብ ለጠባቂዎቹ ከፍለው ወሬው እንዳይሰራጭ ለማድረግ ጥረትን ያደረጉት (ማቴዎስ 28፡ 13) ። አሁንም ደግሞ አስታውሱ፤ ሰዱቃውያኑ ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት አያምኑም ነበረ፡፡
3. የኢየሱስ ከሞት መነሳት ብዙ ሰዎችን አላስደሰተም ነበር፡፡ ጴጥሮስ እየሰበከ/ እያስተማረ የነበረው ምንድን ነው ደግሞም የሰዎቹ ምላሽስ ምን ነበር (የሐዋ 2:32, 37)?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ______________________________________________

4. በሐዋርያት ሥራ 3፡15 ላይ ጴጥሮስ ስለምን እያስተማረ ነበር፤ የህዝቡስ ምልሽ ምን ነበር (ሐዋ 4:2)?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

### ከህይወት ጋር የማዛመጃ ጥያቄዎች

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን የኢየሱስን ከሞት መነሳት ነው፡፡ በሮሜ 10፡9 ላይ እደሚነግረን፡ “ኢየሱስ_______________________ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር

_______________________ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ _______________________ ትድናለህና።"

1. ለዚህ ትምህርት የእናንተስ ምልሽ ምንድን ነው?

   _______________________________________________

   _______________________________________________

2. የኢየሱስ ከሙታን መነሳት ለእናንተ ለአሁኑ ሕይወታችሁ እና ለሚመጣው የእናንተ ከሙታን መነሳት ምን ዓይነት ትርጉምን ይሰጣችኋል?

   _______________________________________________

   _______________________________________________

## ትምህርት

የሚገርመው ነገር በዚህ አለም ውስጥ የሚኖሩ በጣም ብዙ ሰዎች በሙታን ትንሳኤ አያምኑም። በኢየሱስም ትንሳኤም አያምኑም፤ ስለዚህ ለህይወታቸው ምንም ተስፋ የላቸውም ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ይናገራል፤ኢየሱስ ከሞት ባይነሳ ኑሮ ህይወት ምንም አይነት መዓዛና ትርጉም ይኖረው ነበር። 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡ 12-22ን አንብቡ።

1. ጳውሎስ ስለሚሰብከው ስብከት ምን ይናገራል (ቁጥር 14)?

   _______________________________________________

2. ይህ ባይሆን ኖሮ ታድያ ጳውሎስ ስለ እምነት ምን ብሎ ያስተምር ነበር?

   _______________________________________________

   _______________________________________________

3. ጳውሎስ የትምህርቱን ሙግት እንዲህ ባለ መንገድ ሲያጠብቀው ያ ለእኛ ምን ይነግረን ይሆን (ቁጥር 15)?

   _______________________________________________

   _______________________________________________

4. ቁጥር 16 እና 17 መሰረት ስለእነታችን ምን ይነግረናል? _______________________

   _______________________________________________

5. በቁጥር 18 ላይ ጳውሎስ አስቀድመው ሞተው ስለነበሩ ሰዎች ምን ይነግረናል ?

   _______________________________________________

   _______________________________________________

6. በመጨረሻም፤ ጳውሎስ እንደሚለው በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ምን እንሆናለን ነው የሚለን (ቁጥር 19)?

   _______________________________________________

________________________________________________________

ቁጥር 20 ላይ በትልቅ ግን ጳውሎስ ስለሙታ ትንሳኤ እንዲህ ይላል "አሁን ግን ____________ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ____________ተነሥቶአል።" ጳውሎስ የጻፈው እውነታ ምንድነው?

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

## ክፍል 3

**አስተያየት** (የቀጠለ)፡ እስኪ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ የአይሁድ ሸንጎው ፊት ቆመው ተከስሰው ወደ ነበሩበት ታሪክ እንመለስ።

1. ቁጥር 13 የነገሮችን እይታ በመልክ በመልካቸው እንድንይዝ ይረዳናል። ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ፊት ለፊት ተጋፍጠው የነበሩት ሰዎች የተማሩ ነበሩ። የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ናቸው። ህጉን በሚገባ በልቦናቸው ያውቁት ነበር። ይባስም ብሎ አንዳንድ ሌሎችን የራሳቸውን ህጎች ይጨምሩ ነበረ። ይህም በሰዎች ዘንድ ሃይማኖተኛነታቸውን በጉልህ ያሳይ ነበር። አሁን ደግሞ በእነዚህ ህግ አዋቂ ሰዎች ፊት ለፊት የቆሙት ሰዎች ብርቱና እና ጽናት ያላቸው ናቸው። ፅናታቸው ለተሰበሰበው ህዝብ ሁሉ ይታይ ነበረ። ከቁጥር ስምንት አንስቶ በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ የምንመለከተው ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣ የድነትን እውነት ይናገር ነበር። በሰዎቹም እውቀት፣ ዝና እና ስልጣን በፍፁም አልተረበሸም ነበር። ምስክርነትን የሰጠው ስለሚያውቀው እና ስለሚያምንበት ነገር ነበረ። ልክ እየሱስ በሐዋሪያት ስራ 1፡8 ላይ እንደተናገረው ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ እየመሰከረ ነው። የዚህን አይነት ጽናት መቼም ከራሱ ከጴጥሮስ ሳይሆን ከአንድ ከሌላ ወገን እንደመጣ እሙን ነው፣ ምክንያቱም የእነ ጴጥሮስ ከሳሾች ይህ ገብቷቸው ነበር።
   " ጴጥሮስ እና ዮሐንስ__________________________________________ አደነቁ፣__________________ ጋር እንደነበሩ አውቁአቸው" (የሐዋ 4:13)። ያልተማሩ ሰዎች፣ ተራ ሰዎች ብለው ነበር ጴጥሮስን እና ዮሐንስን የገለጹዋቸው።
2. የአይሁድ ሸንጎ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያስገረመው የሚቀጥለው ነገር ደግሞ፣ እነዚህ ሰዎች ማለትም ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ከ ____________አብረው ነበሩ (ቁጥ 13)። ይህንን ነገር ያስተዋለው ማን ነበር? ጴጥሮስን በእሳት ዳር ቆሞ ሳለ ያጋለጠቸው እና ጴጥሮስ ጌታውን በፊቷ ሲኪድ የተመለከተችው ሴት ትኖር ይሆን እንዴ? ወይንስ ጴጥሮስ ጆሮውን የቆረጠው ሰው በዚያ ይኖር ይሆን? የቤተ መቅደሱ ጠባቂ ወይም የካህናቱ አለቃ ወይም ፈሪሳውያኑ

ወይም ኢየሱስን በአታክልቱ ያሰሩት ያሰረቱ ሰዎች በሸንጎው መካከል ኖረው ይሆን? እነኚህ ሁሉ ሰዎች በዚያ የፍርድ ሸንጎ ውስጥ ይኑሩ አይኑሩ ማወቅ ይከብዳል፤ ነገር ግን አንድ ነገር እናውቃለን ይህም እነኚህ ሰዎች እንዲህ ብለው ነበር ______________________________ ______________________________________________________________________________::

**ከህይወት ጋር የማዛመጃ ጥያቄዎች**

በአንድ ጊዜ ሰዎች ሲያገኟችሁ/ ሲገናኙዋችሁ ልክ ለጴጥሮስ እና ለዮሐንስ ያሉትን ነገር ይሏችኋል፤ ማለትም ከኢየሱስ ጋር ነበርክ እንዴ ይሏችኋል?" ሀሳባችሁን ወይንም የገጠማችሁን ነገር ተናገሩ________________________________________________________________________________ ________________________________________________________________________________ ________________________________________________________________________________

**አስተያየት** (የቀጠለ):

1. አሁን የአይሁድ ሸንጎ እና በዚያ ተሰባስበው የነበሩ ሰዎች ሁሉ በእነዚህ በኢየሱስ ተከታዮች ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም ነበር፡፡ ለዚያም ነው እንዲህ ያሉት "እነዚህ ሰዎች ላይ ምን ብናደርግ ይሻላል?" አስታውሱ፤ ከዚህ በፊት ኢየሱስ ተይዞ በተከሰሰ ጊዜ በእርሱ ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ነበር ለሌሎች አሳልፈው ሰጡት፡፡ ወደ ሊቀ ካህናቱ ሐናና ቀያፋ ደጋግመው አምጥተውት ነበር፡፡ ከዚያም ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት ከዚያም ለሔሮድስ፤ ሔሮድስ ደግሞ መልሶ ለጲላጦስ አሳልፎ ሰጠው፡፡ ከዚያም ጲላጦስ ለተሰበሰበው ህዝብ አሳልፎ ሰጠው፤ ታድያ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ላይ ይህንን መሰል ነገር ነው የሚያደርጉት? ችግሩ ምን ነበር (ቁጥር 14 እና 16)?

   ________________________________________________________________________
   ________________________________________________________________________

2. ይህ እጅግ አስቂኝ ነገር ነው፡፡ እነርሱ ይህንን በማድረጋቸው በዚያ አንካሳ ሰው ላይ የተከናወነው የተአምራት ዜናው አይሰራጭም ብለው ገምተው ነበር፡፡ ከዚያም የኢየሱስን ስም እንዳይናገሩ እና እንዳይዛመት ለማቆም አስበው አስጠንቅቀው ሰደዷቸው፡፡ በዚህ ስም እንዳያስተምሩ እና እንዳይሰብኩ አስጠነቀቋቸው፡፡ ነገር ግን አሁንም የጴጥሮስ እና የዮሐንስ ጽናት እና ድፍረት በድጋሚ ተገለጠ፡፡ ምን ብለው የመለሱላቸው ይመስላችኋል (ቁጥር20)?

   ________________________________________________________________

**ከህይወት ጋር የማዛመጃ ጥያቄዎች፡**

1. እናንተ ጴጥሮስን ወይንም ዮሐንስን ብትሆኑ ኖሮ ከመናገር ታቆሙ ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

2. ሰዎች ምን እንደሚያደርጓችሁ የማያውቁበት ጊዜ ገጥሟችሁ ያውቃል፤ ማለትም በኢየሱስ ስም እየተናገራችሁ እያለ ለማስቆም አስበው ያውቃሉ፤ የኢየሱስ ነገር እንዳይስፋፋ?

______________________________________________

______________________________________________

3. ሰዎቹን ዝም እንዲሉ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው? የሰማችሁትን እና ያያችሁትን እውነት እንዳትናገሩ የሚያግዳችሁ ነገር አለን?

______________________________________________

______________________________________________

**ክፍል 4**

***መግቢያ***

*መቼም ይህንን ታሪክ ተከትሎ ምን እንደተፈጠረ ሳንመለከት ጥናታችንን አናቋርጥም። የአይሁድ ሸንጎ ተበተነ፤ ምክንያቱም ባለስልጣናቱ ምን አይነት ውሳኔ ማስተላፍ እንዳለባቸው ግራ ስለገባቸው ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት በተደረገው ተአምራት ሁሉም ሰዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑ እና ይደነቁም ስለነበረ ነው (የሐዋ 4:21-22)። ስለዚህ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ግን ወዴት የሄዱ ይመስላችኋል? ምን የተከሰተባቸውስ ይመስላችኋል?*

**የቤት ስራ፡-** የሐዋ 4:23-41 አንብቡ

***መልመጃ***

1. በቁጥር 23 ላይ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ከአይሁድ ሸንጎ ወደ ወገኖች ሲመለሱ እንመለከታለን "ተፈትተውም ወደ ________________ መጡና የካህናት ________________ ሽማግሌዎች ________________ ሁሉ ነገሩአቸው።"
2. የደረሰባቸውን ሁሉ ሲነግሯቸው የህዝቡ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 24)?

______________________________________________

______________________________________________

3. መጀመርያ የደረሰባቸውን ነገር ከነገሯቸው በኋላ ፀለዩ

ሀ.ለፈጣሪያቸው እውቅናን ሰጡ፤ እንዲህም አሉ

______________________________________________

______________________________________________

ለ. ከቀደምት አባቶቻቸው ከዳዊት የተረዱትም እንዲህ ሲሉ ተናገሩ

አባት ሆይ፤ አንተ ሰማይ እና ምድርን ባህርን እና የብስን ሁሉንም ነገር ፈጠረክ። በመንፈስ ቅዱስም በኩል በባርያዎችህ ተናገርከን፤ ይህንንም በቅዱሱ መጽሐፍህ ውስጥ አገኘን። በቃልህም አማካኝነት በክርስቶስ፤ በጌታ ላይ አንተ በተቀባው ላይ መከራ በህይወቱ ያለፈ መሆኑን ገለጥክልን። ብዙ ሰዎችም በቀባኸው አገልጋይህ በክርስቶስ ላይ ሴራን አሴሩ አገር ግን የአንተ ሃይል አስቀድሞ ሁሉን እንዳቀደ ተከናወነ። አሁንም ጌታ ሆይ ለአንተ ከመለየቴ እና ስለ ኢየሱስ ከመመስከሬ የተነሳ የሰዎችን ማስፈራታቸውን ተመልክተህ እኔን አበርታኝ፤ ይህም ቃልህን በጽናት እና በድፍረት መናገር እችል ዘንድ ነው። እጅህንም ብዙዎችን ለማዳን ትዘርጋ፤ ድንቅ እና ተአምራትህንም በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ ስም በኩል አድርግ።።

## ትምህርት

ይህ ጸሎት የተጻፈው ለእናንተ ነው። ይህም እንዴት የእግዚአብሔርን ቃል መልሰን ለጸሎት እንደምናውል ምሳሌ እንዲሆናችሁ ነው። ይህንንም ጸሎት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ቅዱሳን ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ተመልሰው ሲመጡ የጸለዩት ጸሎት ነው። ለእኛም ህይወት ተመሳሳይ ቃላትን ልንጠቀም እና በህይወታችን ሊሰራብን ይችላል። እግዚአብሄር በሁሉ ላይ፤ በሰማይም በምድርም ላይ ሉዓላዊ አምላክ መሆኑን እውቅናን ይሰጣሉ። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ለአባታቸው ለዳዊት የተናገረውን የተስፋ ቃል ያስታውሳሉ፤ ይህም የተቀባው መሲህ እንደሚሰደድ ነው። ከዚያም ሴራ የሚያሴሩትን ሰዎች ድርጊት ያስታውሳሉ። እነዚህም ልክ በእነርሱ ላይ እንዳሴሩት አይነት ነው። ጸሎታቸው በትልቅ መረዳት እና ድፍረት ነበር። እግዚአብሔርን የሚጠይቁት ይህም እጁን እንዲዘረጋ እና ብዙዎችን እንዲፈውስ እና ብዙ ድንቅ እና ተዓምራትን በኢየሱስ ስም እንዲሆን ነበር።

ይህንን ጸሎት የእለት ተእለት ጸሎታችሁ እንዲሆን አበረታታችኋለሁ፤ እግዚአብሔርም እንዲያበረታችሁ እና በይፋ የቃሉ ተናጋሪ እንድትሆኑ እጁንም ዘርግቶ ብዙዎችን በስሙ እንዲፈውስ እና ብዙ ድንቅ እና ተዓምራትን አንዲያደርግ አብዝታችሁ ጸልዩ።

# ትምህርት አራት

# ሂድ፣ ቁም እና ተናገር

## ከሐዋሪያት ስራ ምእራፍ 4 እና 5 የተወሰዱ ታሪኮች - ወኔ የተሞላበት መታዘዝ

---

ትምህርት አራት

መግቢያ

ክፍልአራት: ሐዋ 4-5

- የጥንቷ ቤተክርስቲያን ህብረት
- ሐናኒያና ሰጲራ
- የጥንቷ ቤተክርስቲያን ልምምዶች
- እንደገና ታሰሩ
- ምስክርነት በቤተ መቅደሱ ደጆች
- በሸንጎው ፊት

## መግቢያ

በክፍል ሶስት የጥንቷን ቤተክርስቲያን ህብረት ተመልክተናል። ህብረታቸው ሲገለጥ የነበረው በሚኖሩት የህይወት ዘይቤ ነበር። የሐዋሪያት ስራ ምእራፍ አራት እንደሚነግረን ያመኑት አንድ ልብና ሀሳብ እንዲኖራቸው  በጣም ይጥሩ ነበር። ያላቸው ነገር ሁሉ እንዴት ለጋራ ጥቅም እንደሚውል ያስቡ ነበር። ህይወታቸውም በአጠቃላይ የህብረት ህይወት ነበር። ምእራፍ 4 ቁጥር 32-37 ስታጠኑ የዛሬይቱ ቤተክርስቲያን ደግሞ በምን ሁኔታ አንድነቷን እንዲሁም የህብረት ህይወቷን ልትገልጥ እንደምትችል አሰብ አድጉ።

ለምንድነው ሐናኒያና ሰጲራ እንደዚህ አይነት ፍርድ የተቀበሉት?  የዚህ አይነት ፍርድ ለምን አስፈለገ? የሐናኒያና ሰጲራ ድርጊት የጌታ "ምስክሮች" በሆኑት ህብረተሰብ የጋራ ህይወት ወይም ህብረት ላይ ምን አይነት አደጋ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችል ነበር? እንዲህ አይነቱ ማጭበርበር የዛሬይቱን ቤተ ክርስቲያን በምን መልኩ ሊጎዳት እና በምን አይነት አደጋ ሊበክላት ይችላል?

አንድ ሰው "በእርግጥ እነዚህ ሰዎች ከስህተታቸው ሊታረሙ አይችሉም ነበር?" ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። ሐዋሪያቱ በድጋሜ ታስረው በገዢዎችና በባለ ስልጣናት ፊት ቆመው ነበር። እርግጥ ነው በቤተ መቅደሱ አደባባዮች በድፍረት ከመመስከር ራስን መሸሸግ ይሻላል። ነገር ግን እየሱስ እንዲህ ብሎ ደቀ መዛሙርቱ ባሉበት ተናግሯል "ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነገር ግን ነፍሱን ስለ እኔ የሚያጠፋ የሚያጠፋት ያድናታል።" ማቴ 16፡ 24

## ትምህርት አራት

### ክፍል አንድ ፡ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ህብረት

***መግቢያ፡***

በትምህርት ሁለት ክፍል አንድ እንደተመለከትነው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ልምዶች በሐዋ 2፡ 42-47 ተጠቅሷል። የሐዋሪያት ስራ ፀሐፊ ቅዱስ ሉቃስ በሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ታሪኮች ከመንገሩ በፊት የጌታን ከሞት መነሳትና ማረግ የመሰከረችውን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ልምዶች ይነግረናል።

**የቤት ስራ፡** የሐዋ 4፡ 32-36 አንብቡ።

***መልመጃ***

1. ቁጥር 32 ስለ አማኞች ምን ይነግረናል?

 ____________________________________________________________

2. በቁጥር 32 ላይ የተመለከትነው የሀሳብና የነፍስ አንድነት በምን በምን ይገለጻል?

 ____________________________________________________________

 ____________________________________________________________

3. ስለ ክርስቶስ ትንሳኤ መመስከር በመሪዎች ህይወት ላይ መከራ አስከትሎ ነበር። ለምሳሌ ዮሐንስና ጴጥሮስ ታስረው ነበር። በተጨማሪም በዚህ ስም እንዳይመሰክሩ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ነበር (ሐዋ 4፡18)። በዚህ ጉዳይ ላይ ሐዋሪያት ስለ ወሰዱት እርምጃ ቁጥር 33 ምን ይነግረናል?

 ____________________________________________________________

 ____________________________________________________________

 ስለ ክርስቶስ ትንሳኤ መመስከራቸውን ከመቀጠል አልፈው ______________________ እና__________________ይመስክሩ ነበር።

4. በቁጥር 20 ላይ ሐዋሪያቱ ለሀይማኖት መሪዎች ምን ብለው መለሱ?

 ____________________________________________________________

 ____________________________________________________________

5. የእግዚአብሔር መገኘት ከእነርሱ ጋር ነበር። ቁጥር 33 በሁሉም ላይ____________________ ነበረባቸው ይላል።

6. ስለ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንድነት እና ያላቸውንም ንብረት ለማካፈል ስለነበራቸው ልግስና ተመልክተናል። ኢየሱስ ከሙታን ስለመነሳቱ የሰጡትንም የማያቋርጥ ምስክርነት ተምረናል።

የእግዚአብሔርም ጸጋ በሁሉ ላይ ነበረ። ቁጥር 34 እና 35 ስለ ጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ልምድና ባህሪይ ይነግረናል። እነዚህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ልምድና ባህሪይ ምን ምን ናቸው?

____________________________________________________________

_________________________________________________________

7. በመቀጠል ቁጥር 36-37 በተለየ መልኩ ስለ አንድ ሰው ያወሳል። ይህ ሰው ማን ነው?

__________________________________________________________

ስለ እርሱስ ምን ተነገረን?

____________________________________________________________

_________________________________________________________

__________________________________________________________

## ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች

1. አንድነት ወይም ህብረት የተሞላበት የአማኞች ስብስብ ምን አይነት ባህሪያት ይኖሩታል? በእግዚአብሔር ህዝብ መካከል ግጭትና መከፋፋል በተደጋጋሚ የሚከሰት ነገር ሆኗል። ምንም እንኳን መለያየትና መከፋፈል የተለመደ ነገር ቢሆንም የሚያስፈልገን ግን አንድነትና ህብረት ነው። በግልህ/ሽ የህብረትን አንድነት ተለማምደህ ታውቃለሁ? በልብና በነፍስ አንድ በመሆን ውስጥ የሚገኙ በረከቶች ምን ምን ናቸው?

   በሚከተሉት የግንኙነት ውስጥ አንድነትን ለማሳደግ ምን ምን እንዲደረግ ትሞክሪያለሽ/ለህ

   ሀ. በትዳር ውስጥ

   ____________________________________________________________

   _________________________________________________________

   ለ. በቤተሰብ ውስጥ

   ____________________________________________________________

   _________________________________________________________

   ሐ. በስራ ቦታ/በቢሮ ውስጥ

   ____________________________________________________________

   _________________________________________________________

   መ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

   ____________________________________________________________

   _________________________________________________________

2. አንተ ባለህበት ህብረት ውስጥ በርናባስ የተጫወተውን ሚና በመጫወት በህብረቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች ባለህ/ሽ መንፈሳዊ ስጦታ በመጠቀም እንዴት መጽናናትንና ማበረታታትን ልትሰጥ/ጭ ትችያለሽ?

________________________________________________________

________________________________________________________

____________________________________________________

**ክፍል ሁለት፡ ሐናኒያና ሰጲራ**

**የቤት ስራ፡** ስለ ሐናኒያና ሰጲራ የሚተርከውን ክፍል፤ ሐዋ 5፡ 1-11 አንብቢ/ብ፡፡

በርናባስ በአንድ ልብና ነፍስ ከነበሩት አማኞች ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ በዚህ ክፍል ላይ ያለው ታሪክ እንደ በርናባስ ያሉ በአንድ ልብና ነፍስ የነበሩት አማኞች ለማታለል ስለሞከሩ ባልና ሚስት ይተርካል፡፡

**መልመጃ፡**

1. በቁጥር አንድ መሰረት ሐናኒያና ሰጲራ ምን አደረጉ?

   ________________________________________________

2. በቁጥር ሁለት መሰረት ሐናኒያ በገንዘቡ ምን አደረገ?

   ______________________________________________________

   __________________________________________________

3. በቁጥር ሁለትና ሦስት መሰረት ሰጲራ ከመሬቱ ሽያጭ ስለተገኘው ብር እናም ለሐዋሪያት ሊሰጥ ስለታሰበው ብር ምን ያህል መረጃ?

   ___________________________________________________

   ___________________________________________________

4. በቁጥር ሦስት መሰረት ጴጥሮስ ሐናኒያን በምን በምን ተጠያቂ እንዳደረገው በሚከተሉት መንገድ ለመመለስ ሞክር፡

   ሀ. የሐናኒያን ልብ የሞላው ማን ነው?

   ______________________________________________________

   __________________________________________________

   ለ. በልቡ የሞላው ምክር ምን እንዲያደርግ አነሳሳው?

   ______________________________________________________

   __________________________________________________

ሐ. ከመዋሸት ባለፈ ምን አደረገ?

_______________________________________________________________

_________________________________________________________

5. ከክፍሉ እንደምንረዳው ጴጥሮስ ሐናኒያን የመሬት ባለቤት በመሆኑ አልወቀሰውም። መሬቱን አሊያም ንብረቱን ሲሸጥ ባገኘው ገንዘብ ምክንያትም ተጠያቂ አላደረገውም። የሐናኒያ ውሸት ምን ነበር? ጴጥሮስ "ለመሆኑ ይህን ነገር እንዴት_____________አሰብህ? የዋሸኸው እኮ____________ እንጂ______________አይደለም።" አለው።

6. ሐናኒያ ያጠፋው ምንድን ነው?

_______________________________________________________________

_________________________________________________________

____________________________________________________________

7. በቁጥር አምስት መሰረት ሐናኒያ ምን ሆነ?

____________________________________________________________

8. በቁጥር አምስት መሰረት ይህንን ጉዳይ የሰሙት ላይ ምን ደረሰ?

____________________________________________________________

9. በቁጥር ስድስት መሰረት ሐናኒያን ተሸክመው አወጡትና ቀበሩት። በቁጥር ሰባት መሰረት ከሦስት ሰአታት በኂላ ምን ተከሰተ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

10. በቁጥር ስምንት መሰረት ጴጥሮስ ሰጲራን ምን ጠየቃት?

___________________________________________________

11. እርሷስ ምን ብላ መለሰች?

____________________________________________________________

12. በመቀጠል ጴጥሮስ "የጌታን መንፈስ________________ትፈታተኑ ዘንድ እንዴት እንዲህ ተስማማችሁ?" ብሎ ጠየቃት።

13. ስለእርሷስ በቁጥር ዘጠኝ ላይ ጴጥሮስ ምን ተናገረ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

14. ጴጥሮስ ሲናገር ምን ሆነ?

_______________________________________________________________

_________________________________________________________

ጉልማሶቹም ምን አደረጉ?

15. ስለ ቤተ ክርስቲያን እና ነገሩን ስለ ሰሙ ሰዎች ክፍሉ ምን ይለናል?

**የማሰላሰያ ነጥብ፡**

ይህ ታሪክ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስን እና ሰዎችን ስላሳዘነ ኃጢአት ይተርክልናል። ሐናኒያና ሰጲራ እያወቁ ፈቅደው ቤተ ክርስቲያንን እና እግዚአብሔርን ዋሹ። በእውነት መሬታቸውን የሸጡበት ዋጋና እነርሱ የተናገሩት ዋጋ የተለያየ ነበር። በዚህ ምክንያት አስመሳዮች ናቸው ልንላቸው እንችላለን።

1. ለምን ይሆን ይህ ኃጢአት ሊገዝፍ የቻለው? ቅጣቱስ የሞት ቅጣት የሆነበት ምክንያት ምን ይሆን?

2. ማታለል ወይም መዋሸት በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያደርስው እንዴት ነው?

**ፀሎት**

እግዚአብሐር ሆይ ሐናኒያና ሰጲራ የተፈተኑበት ፈተና ዛሬም የኔ ፈተና ነው። እኔም እንደ እነርሱ ምንም እንኳን ውስጤ ኃጢአት ቢኖርም ጥሩ ሰው የሆንኩ ለማስመሰል እጥራለሁ። ለሰዎች ጥሩ ሰው መስዬ ለመታየት ስል እዋሻለሁ። ስለዚህም፣ አምላኬ ሆይ ይቅር በለኝ። አንተ ብቻህን ጥሩ ሰው እንድሆን እና በሰዎች ፊት ተቀባይነት እንዲኖረኝ እንደምታደርግ እንዳምን እርዳኝ። አንተ ብቻህን ንጹህ ልብ እና ቀና መንፈስ ልትፈጥርልኝ ትችላለህ። በሰማያዊው አባቴ ፊት በድፍረትና በልበ ሙሉነት እንድቆም የሚረዳኝ የአንተው በጎነት ብቻ እንደሆነ እንዳምን እርዳኝ።

**ክፍል ሦስት፡ የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን ልምድዶች**

**ትምህርት**

በሐዋ 5፡ 12-16 በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስለተመሰረቱ አንዳንድ ስርአቶች እንማራለን።

1. ቁጥር 12 ስለ ሐዋሪያቱ ምን ይነግረናል?

_______________________________________________

_______________________________________________

2. ቁጥር 13 ያመኑት ሁሉ ምን ያደርጉ እንደ ነበር ይለናል?

_______________________________________________

3. ቁጥር 14 ምን ይነግረናል?

_______________________________________________

_______________________________________________

4. በመቀጠል ቁጥር አስራ አምስት አዲስ ነገር ይነግረናል። ይህ ቁጥር ምን አዲስ ነገር ያስተላልፍልናል?

_______________________________________________

_______________________________________________

5. ሰዎች የታመሙትንና በክፉ መንፈስ የሚሰቃዩን ወደ ሐዋሪያቱ ያመጡ ነበር። ስለእነዚህ ሰዎች ቁጥር 16 ምን ይነግረናል?

_______________________________________________

_______________________________________________

6. ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስለ በሽተኞች መፈወስ ምን ልንማር እንችላለን?

_______________________________________________

_______________________________________________

7. በእየሩሳሌም አካባቢ ከሚገኙ ከተሞች ስለሚመጡት ሰዎች ቁጥር 16 ምን ምን ያሳየናል?

_______________________________________________

_______________________________________________

**መግቢያ**

በሚቀጥለው ታሪክ እንደምንመለከተው መከራ ወደ ሐዋሪያቱ መምጣት ይጀምራል። ሊቀ ካህኑ እንዲሁም ከእርሱ ጋር የነበሩ ሁሉ______________________________ይሞላሉ።

ይህ አይገርምም፤ በሐዋ 4፡8 እና 31 እንደምናነበው ጴጥሮስና ሌሎችም ሰዎች በ__________________________ይሞላሉ። በቅንአት የተሞሉት ሐዋሪያቱን ፀጥ ለማሰኘት ሰዎችን ማሰር ይጀምራሉ። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት የእግዚአብሔርን ቃል በሀይል ይናገራሉ።

**የቤት ስራ፡** ሐዋ 5፡ 17-42 አንብቡ።

**መልመጃ፡**

1. ሐዋሪያቱ ታስረው በወህኒ በተጣሉበት ለሊት ምን ሆነ (ቁጥር 19-20 አንብቡ)?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. በቁጥር 21 መሰረት ሐዋሪያቱ ምን እርምጃ ወሰዱ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3. ከላይ በተጠቀሰው ቁጥር ላይ በመቅደሱ አደባባይ የተሰበሰበው ህዝብ ማን ነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

4. ሊቀ ካህናቱ እና ከእነርሱ ጋር የነበሩት ሐዋሪያቱን ለማስጠራት ወደ እስር ቤት መልእክተኞች ሲልኩ የገጠማቸው ነገር ምን ነበር?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

5. መልእክተኞቹ ምን መልስ ሰጡ (ቁጥር 23 አንብቡ)?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

6. የሐይማኖት መሪዎቹ በቁጥር 24 መሰረት ምን ተሰማቸው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ወህኒ ቤቱ በጥንቃቄ የተዘጋ እና በጠባቂዎችም የሚጠበቅ ነበር። ስለዚህ የሐዋሪያቱ ከእስር ቤት ማምለጥ የማይገመት ነገር ነበር።

7. በሆነው ነገር ምክንያት ሰው ሁሉ በመደነቅ እና በመገረም ተሞልቶ ነበር። የበለጠ የሚገርመው ደግሞ አንድ ሰው ወደ ሐይማኖት መሪዎቹ መጥቶ ታስረው የነበሩት ሐዋሪያት በጊዜው የት እንደሚገኙ መናገሩ ነው። በተናጋሪው መሰረት ሐዋሪያቱ የት ነበሩ?

8. ምንስ እያደረጉ ነበር?

9. የጥበቃ ሹሙም ከወታደሮች ጋር ሐዋሪያቱን አመጣቸው። በቁጥር 26 መሰረት እንዴት አመጣቸው?

## ክፍል አራት፡ እንደገና ታሰሩ!

1. ይህ ታሪክ የሐይማኖት መሪዎች ህዝቡን ወደ መፍራት እንደጀመሩ ይተርካል። ይህ ደግሞ የሚገርም የታሪክ ክስተት ነው። ቀጥሎ በተዘረዘሩት ክፍሎች ውስጥ የሐይማኖት መሪዎች እንዴት እንደተገለጽ ልብ በሉ

   ሀ. ሉቃስ 22፡ 2

   ለ. ማርቆስ 11፡18

   ሐ. ማቴዎስ 26፡4-5

2. የሐዋሪያት ስራ ከተናወነበት ጊዜ ሁናቴ ተነስተን ስንናገር የሐይማኖት መሪዎች ስልጣን ስለነበራቸው ሐዋሪያቱ ሊፈሯቸው ይገባ ነበር። ሐዋሪያቱ ለእስር የበቁት ኢየሱስን ባስገደሉት ባለ ስልጣናት ነው። ስለዚህም ፍርሀት ሊያድርባቸው ይገባል። ነገር ግን በሐዋ 5፡20 መሰረት “ሂዱ፤ በቤተ መቅደሱም አደባባይ ቁሙ፤ የዚህንም የህይወት ቃል ሁሉ ለህዝቡ ንገሩ” የሚል ትእዛዝ ተቀብለው ነበር። እናም የታዘዙትን አደረጉ። በቀንም ወደ ዚህ አደባባይ እየመጡ ህዝቡን ያስተምሩ ነበር። ድፍረታቸውን እናም ወኔያቸውን እንዴት

ትገልጸዋለህ? በዮሐንስ ወንጌል 20፡9 መሰረት እነዚሁ ሰዎች ________________________ ፈርተው ተደብቀው ነበር። አሁን ታዲያ ምን ነካቸው ትላለህ/ያለሽ?

________________________________________________

________________________________________________

**የትግበራ ጥያቄ**

1. በቁጥር 27 መሰረት ሐዋሪያቱን በሸንጎ ፊት አቆሟቸው። የተከሰሱበት ነጥብ ምን ነበር (ቁጥር 28ን አንብቡ)?

________________________________________________

________________________________________________

2. የጴጥሮስ መለስስ ምን ነበር (ቁጥር 29ን አንብቡ)?

________________________________________________

________________________________________________

3. በቁጥር 30 መሰረት የጴጥሮስ መልስ ማንን እንዲያስታውሱ ይረዳል?

________________________________________________

4. በቁጥር 31 መሰረት የክርስቶስ ከሞት መነሳት ምንን ይሰጣል?

________________________________________________

________________________________________________

5. በቁጥር 32 መሰረት ምስክርነት የሚሰጡት እነማን ናቸው?

________________________________________________

6. የሐይማኖት መሪዎቹ ይህንን ሲሰሙ ምን ተሰማቸው? ምንስ ማድረግ ፈለጉ?

________________________________________________

________________________________________________

7. ገማልያል ማን ነው?

________________________________________________

8. ገማልያል ከሸንጎው ጋር ተነጋገረ። ገማልያል ከቁጥር 35-39 የተናገረውን በራሳችሁ አባባል ግለጹት።

________________________________________________

________________________________________________

9. የገማልያልን ንግግር ከሰሙ በኋላ የሐይማኖት መሪዎቹ ምን እርምጃ ወሰዱ?

________________________________________________

10. ከቁጥር 41-42 ያለውን አንብብ፡፡ በዚህ ንባብ መሰረት የሐዋሪያቱ መልስ ምን ነበር?

ሀ.__________________________________________________________________

______________________________________________________________

ለ.__________________________________________________________________

______________________________________________________________

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች**

1. ሐዋሪያቱ መደረሰባቸው መከራ ደስተኞች ነበሩ፡፡ መልካሙን ዜና እርሱም ክርስቶስ ጌታ መሲህ እንደሆነ መመስከር አላቆሙም ነበር፡፡ ከሐዋሪያቱን ህይወት በመመልከት ስለ ወንጌል መከራን ለመቀበል ምን ያህል ዝግጁ ነኝ፡፡ ምንም እንኳን መከራ ቢኖር መከራውን ለመጋፈጥና በድፍረት የክርስቶስን ወንጌል ለማዳረስ ምን ያህል ዝግጁ ነኝ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________________________________________________________

2. "በቤተ መቅደሱም አደባባይ ቁሙ፤ የዚህንም የህይወት ቃል ሁሉ ለህዝቡ ንገሩ" የሚለው ትእዛዝ ዛሬ ለእኔ እንደሆነ አስባለሁ? ዛሬ ወንጌልን የምስብክበት የመቅደሱ አደባባይ የቱ ነው?

______________________________________________________________

____________________________________________________________

**ፀሎት፡**

ጌታ ኢየሱስ ሆይ ሐዋሪያትህን በወኔና በድፍረት የተሞሉ የአንተ መስካሪዎች እንዲሆኑ በሀይል ስላስታጠካቸው አመሰግንሀለሁ፡፡ ከሰው ይልቅ አንተን ሰምተው ታዘዋል፡፡ የሰሙትን እና ያዩትን ለመናገር ጨክነው ነበር፡፡ መታሰርን፣ መከራ መቀበልን፣ ወይም መገፋትን ከመፍራት ይልቅ የአንተን ትእዛዝ መከተልን መርጠው ነበር፡፡ ስለዚህም በመቅደሱ አደባባይ በድጋሚ ተገኝተው ይህንን አዲስ ህይወት ለህዝቡ ማስተማር ችለው ነበር፡፡ እኔም በእነርሱ ጎዳና በመጓዝ ለአንተ ታማኝ እንድሆን እርዳኝ፡፡ እኔም በመከራ ውስጥም ቢሆን ህይወቴ የአንተን ህይወት እንዲሁም ለሰዎች ሁሉ ያሳየህውን በጎነት እንዲመሰክር እርዳኝ፡፡ ስለአንተ ያየሁትን፣ የሰማሁትን እና የቀመስኩትን እንድመሰክር በሀይልና በድፍረት አስታጥቀኝ፡፡

______________________________________________________________________

# ትምህርት አምስት

# እምነት የሞላበት ሰው

## የሐዋሪያት ስራ ምእራፍ 6 -8
## ሰማእታቱ እሲጢፋኖስ

---

### የትምህርት አምስት

*መግቢያ*

ጥናት አምስት: ሐዋ 6-8

- የእስጢፋኖስ ለማህበራዊ አገልግሎት መጠራት
- እስጢፋኖስ እና ከሳሾቹ
- የእስጢፋኖስ ስብከት መቀጠል
- የማሰላሰያና ከህይወት ጋር የማዛመድ ነጥቦች
- ፊሊጶስ እና ስምኦን
- ጴጥሮስ እና ስምኦን

## መግቢያ

የጥንቷን ቤተክርስቲያን የማህበራዊ አገልግሎት የበዛባት ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡፡ ይህንን የአገልግሎት ዘርፍ የሚያገለግሉ ሰዎችን የሚመድቡት ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ፡፡ በዚህ አገልግሎት ላይ ሰዎችን ለማሰማራት መስፈርትን አውጥተው ነበር፡፡ እነዚህን መስፈርቶች ለመፃፍ ሞክሩ፡፡ የሰዎችን ፍላጎት ለማገልገል የመረጧቸው ፤አገልጋዮች እነዚህ መስፈርቶች እንዲኖራቸው የተፈለገው ለምን ይመስላችኋል፡፡ ዛሬ አንተ/አንቺ ብትሆኚ እነዚህን መስፈርቶች የምታወጣው/ጪው ምን ምን መስፈርቶች ትመርጥ/ጪ ነበር? የአንተ/የአንቺ መስፈርትና የደቀ መዛሙርቱ መስፈርቶች ተመሳሳይነት አላቸው?

እስጢፋኖስ በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ የተዋጣለትን ስራ እየሰራ ነበር፡፡ ነገር ግን በተጎዳኝ የሚያገለግለው አገልግሎት የብዙዎችን ልብ መሳብ ችሎ ነበር፡፡ እስጢፋኖስን ለማስወገድ ከሳሾቹ ምን ምን እርምጃዎችን ወስደው ነበር?የእስጢፋኖስ ክስ ከማን ክስ ጋር ይመሳሰላል? ስለ ተከሰሰበት ክስ እንዲያብራራ መጠየቁን ስለ ክርስቶስ ለመመስከር የተሰጠው እድል አድርጎ መቁጠሩ የሚገርም ነው፡፡

የቅዱስ እስጢፋኖስ መልስ ጴጥሮስ በአንደኛ ጴጥሮስ 3፡15 ላይ "በእናንተም ስላለች ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁልጊዜ ተዘጋድታችሁ ኑሩ፡፡" ተብሎ የተፃፈውን ያስታውሰናል፡፡ እስጢፋኖስ ለከሳሾቹ የሰጠውን መልስ በጥሞና ተመልከቱ፡፡ በመልሱም የእስራኤላዊያንን ታሪክ የተረከ ሲሆን በሚከተለውም ስንኞች መልሱን ቋጭቷል "እናንተ አንገታችሁ የደነደነ፣ ጆሮአችሁም የደነቆረ፣ እንደ አባቶቻችሁ መንፈስ ቅዱስን ዘወትር ትቃወማላችሁ፡፡" እነዚህም ድፍረት እና ወቀሳ የሞላባቸው ስንኞች ከሳሾቹ እስጢፋኖስን በፍጥነት ከከተማ አውጥተው እንዲወግሩት አድርጓል፡፡

## ትምህርት  አምስት

### ክፍል አንድ ፡ የእስጢፋኖስ ለማህበራዊ አገልግሎት መጠራት

**መግቢያ**

በቀጣዩ ታሪክ በስራ የተጠመደች ቤተ ክርስቲያንን እንመለከታለን፡፡ ክርስትና አንድ አማኝ በግሉ ከእግዚአብሔር ጋር በሚያደርገው ህብረት ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ማንኛውም አማኝ በክርስቶስ የአመኑ ሰዎች ህብረት አካል ነው፡፡ እግዚአብሔር በአመኑ ሰዎች ህብረት ውስጥ የሚያፈሰው ፍቅር በህብረት ውስጥ  አልፎም ከህብረቱ ውጭ ያሉትን ሰዎች ጉድለት ለመሙላት ያገለግላል፡፡ ይህ ተግባሯ ቤተ ክርስቲያንን ንቁና ሥራ የሞላባት ያደርጋታል፡፡ በሐዋ 6 ላይ እንዲህ አይነቷን ቤተ ክርስቲያን እንመለከታለን፡፡

**የቤት ስራ፡**  የሐዋ 6፡ 1-7 አንብቡ፡፡

**መልመጃ**

8. በቁጥር 1 መሰረት በቤተ ክርስቲያን ምን አይነት ችግር ተከሰተ

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

9. አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ደቀ መዛሙርትን ወይም ያመኑትን ሰብስበው ችግሩን ተወያዩ
   ሀ. በቁጥር 2 መሰረት የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ሐላፊነት ምንድን ነው ?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

   በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ያመኑ ሰዎች የነበራቸውን ድርሻ በሚገባ አጤኑ፡፡ ሐዋሪያቱ ቃሉን ለማስተማር ወስነው ነበር፡፡ ነገር ግን ቃሉን ከመስበክ ስራ ባሻገር በማኅበራዊ አሊያም በማእድ አገልግሎት የሚያገለግሉ ሰዎች ያስፈልጉ ነበር፡፡ ሁለቱም አገልግሎቶች አስፈላጊ ናቸው፡፡ ሁለቱም የተለያዩ ስጦታዎች ይጠይቁ ነበር፡፡

   ለ. በ ቁጥር ሦስት መሰረት ከ ______________________________ ውስጥ ______________________________የመምረጥ ሀላፊነት ለደቀ መዛሙርቱ ተሰጣቸው፡፡

10. ለማእድ አገልግሎት የተመረጡ ሰዎች በቁጥር 5 ላይ ተዘርዝረዋል፡፡ ከተመረጡት ሰዎች ውስጥ በአንደኝነት ስሙ የተፃፈልን

_______________________________________________ ነው። በዚህ ቁጥር መሰረት ይህ ሰው ምን አይነት ሰው ነው?

_______________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

11. በቁጥር አምስት ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች _________________________ ፊት አቆሙዋቸው። በመቀጠል ለእነዚህ ሰዎች ምን ተደረገ?________________________________________

_____________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________________

12. ከቁጥር 1-6 በተከናወነው ስራ መሰረት ሶስት ውጤቶች ተገኝተዋል። ውጤቶቹን ዘርዝር።

_____________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

**የማሰላሰያ ነጥብ**

ያለንን ስጦታ አሳንሶ መመልከት በአማኞች ህብረት የተለመደ ነገር ነው። በተለይም የመስተንግዶ ወይም በማእድ የማገልገልን ስጦታ አሳንሰን እንመለከታል። በዚህ ታሪክ ውስጥ በቃልና በጸሎት ሆነ በመስተንግዶ ማገልገል ለወንጌሉ መስፋፋት ተርፎም ለምእመናን ጤናማ መንፈሳዊ እድገት በጣም አስፈላጊ ስጦታዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ለማደግና የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስፋት ትችል ዘንድ የእያንዳንዱን አባል መንፈሳዊ ስጦታዎች መጠቀም ያስፈልጋታል፡

**ጥያቄ፡** ያደግንበት ሁኔታ የተለያየ ችሎታ እንዲኖረን ትልቅ አስተዋጽኦ ይጫወታል። በተጨማሪም መንፈሳዊ ስጦታዎችም ይኖሩናል። እነዚህን ችሎታዎችና መንፈሳዊ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዴት መጠቀም እንችላለን?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________________

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች**

1. ይህ ጥናት እኔ ለቤተ ክርስቲያን አልፎም ለሌሎች ሰዎች የምስጠውን አገልግሎት በምን መልክ ይቃኛል ወይም ምን ያስተምረኛል?

2. በቤተ ክርስቲያን ያለኝን አገልግሎት እንደ ስራዬ እመለከተዋለሁ? በየትኛውም አገልግሎት ብሰማራ ወንጌልን መስበክና መንግስቱን ማስፋት ተጨማሪ ስራዬ ነው የሚል እምነት አለኝ? ይህን እምነትም በተግባር ለሰዎች በመመስከር እኖረዋለሁ?

3. ምን አይነት የህይወት ለውጦች ያስፈልጉኛል?

   ሀ. በስራ ቦታዬ

   ለ. በአስተሳሰቤ

   ሐ. ችሎታዎቼንና መንፈሳዊ ስጦታዎችን መመጠቀም አቅጣጫ

   መ. በተለያዩ ግንኙነቶቼ

3. አንተ ባለህበት ህብረት ውስጥ በርናባስ የተጫወተውን ሚና በመጫወት በህብረቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች ባለህ/ሽ መንፈሳዊ ስጦታ በመጠቀም እንዴት መጽናናትንና ማበረታታትን ልትሰጥ/ጭ ትችያለሽ?

**የማሰላሰያ ነጥብ**

በቁጥር ሰባት ላይ በተጠቀሱት ውጤቶች ላይ አሰላስል፡፡ እግዚአብሔር እስጢፋኖስንና ሌሎችንም እንዴት ለአገልግሎቱ እንደተጠቀመ አስብ፡፡ መሪዎቹ ለማእድ ስራ የተመረጡ ሰዎችን መልካም ስምና በጎ ባህሪይ ተመልክተው ነበር፡፡ የተመረጡትም መንፈስ ቅዱስ እና ጥበብ የሞላባቸው ተብለው ነበር፡፡

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች**

16. ሰዎች ስለ እኔ ምን ያውቃሉ? በጎረቤቶቼ፣ በቢሮዬ እናም በተደጋጋሚ በምውልባቸው ቦታዎች ላይ ያለኝ ስም ምን ይመስላል? ወይም ሰዎች ስለ እኔ ምን ያስባሉ? ስለ ባህሪዬ ቢጠየቁ ሰዎች ምን ይመልሳሉ?መንፈስ ቅዱስ እና ጥበብ የተሞላ/ች ናት/ነው ይሉ ይሆን?

______________________________________________

______________________________________________

17. ባህሪዬ እግዚአብሔርን ያንጸባርቃል?ወይስ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲለውጠኝ እፈልጋለሁ? ምን ምን አይነት ለውጦች ያስፈልጉኛል?

______________________________________________

______________________________________________

**ክፍል ሁለት፡ እስጢፋኖስ እና ከሳሾቹች**

**የቤት ስራ፡** የእስጢፋኖስ ታሪክ ቀጥሏል፡፡ የሐዋ 6፡ 8-15 አንብቡ፡፡

**መልመጃ**

8. ስለ እስጢፋኖስ በተለየ መልኩ የሚነግረን ቁጥር 8 ነው፡፡ ይህ ቁጥር ስለ እስጢፋኖስ ምን ይነግረናል?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

9. በቁጥር 9 መሰረት______________________________እና

______________________________________________

______________________________________________

እስጢፋኖስን ይከራከሩት ነበር፡፡ ቁጥር 10 ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ምን ይለናል?

______________________________________________

______________________________________________

10. በቁጥር 11 መሰረት በክርክር ሊረቱት እንደማይችሉ ሲገባቸው ምን አደረጉ?

______________________________________________

______________________________________________

11. በቁጥር 12 ላይ የተሰጠው የሐሰት ምስክርነት ምን አስከተለ?

ሀ. በቁጥር 12

______________________________________________

ለ. በቁጥር 13

______________________________________________

ሐ. በቁጥር 14

______________________________________________

______________________________________________

**ማስታወሻ፡** ቤተ መቅደሱ እና ህጉ በሙሴ ህግ መስረት የተቀደሱ ናቸው። አይሁዳዊያን እና የሀይማኖት መሪዎቻቸው የተቀደሱ አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር።

12. በሸንጎ የተቀመጡ ሰዎችም የእስጢፋኖስን ፊት ተመለከቱት። ፊቱ ምን ይመስል ነበር ?

______________________________________________

______________________________________________

---

## ክፍል ሦስት፡ የእስጢፋኖስ ስብከት መቀጠል

**መግቢያ፡**

በሐዋ 7፡ 2-53 መሰረት የሀይማኖት ሸንጎው እስጢፋኖስን "ይህ ሰው እግዚአብሔርን ይሳደባል" ብለው ከሰውቷል። በምእራፍ ሰባት ቁጥር አንድ ላይ ሊቀ ካህናቱ "ይህ ክስ እውነት ነውን?"የሚል ጥያቄ ለእስጢፋኖስ ያቀርብለታል። እስጢፋኖስም ይህን ጥያቄ ለመመለስ የተሰጠውን እድል ስለ ክርስቶስ የመመስከሪያ እድል አድርጎ ቆጠረው። የእስጢፋኖስ መልስ ከአብርሀም እስከ ኢየሱስ ያለውን የእስራኤላዊያንን ታሪክ የያዘ ነበር። እግዚአብሔርም የታሪክ ሁሉ ባለቤት እንደሆነ ይህ ትርካ በሚገባ ያስረዳል። እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ሰውን ይፈልግና እርሱ በመረጠው ሳው አማካኝነት ህዝብን ያድን ነበር። አምላካችን አብርምን ወደ ከነአን ሙሴን ደግሞ ወደ ተስፋይቱ ምድር ልኳል። ይህም

የሚያሳየን ለራሱ አላማ ሰዎችን እንደሚልክ፤ እንደሚያሰማራ ነው። ትላንት ነቢያትን አልፎም ልጁን ልኮ ነበር። ዛሬ ደግሞ እኛን ይልከናል።

**የቤት ስራ፡** ሐዋ 7፡ 2-53 አንብቡ።

**መልመጃ፡ ቁጥር 2-8**

10. የዚህ ክፍል ዋና ገጸ ባህሪ ማን ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

11. በቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ምንድን ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

12. እግዚአብሐር የት ነው የላከው?

_______________________________________________

13. በቁጥር 5 መሰረት እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ምንድን ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

14. እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገረው ነገር ምንድን ነው (ቁጥር 6-7 አንብቡ)?

_______________________________________________

_______________________________________________

15. እግዚአብሔር ከአብርሀም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ምንድን ነው (ቁጥር 8 አንብቡ)?

_______________________________________________

_______________________________________________

16. ቁጥር 8ን በድጋሚ እንመልከት፤

ሀ. በዚህ ቁጥር መሰረት ልጁ ማን ነው?

_______________________________________________

ለ. በዚህ ቁጥር መሰረት የልጅ ልጁስ ማን ነው?

_______________________________________________

**መልመጃ ፡ ከቁጥር 9-19**

1. የዚህ ክፍል ዋና ገጸ ባህሪ ማን ነው?

_______________________________________________

2. እግዚአብሔር ራሱን ለዮሴፍ የገለጠው እንዴት ነው (ቁጥር 10 አንብቡ)

_______________________________________________

3. በቁጥር 11-16 መሰረት የተነሳው ድርቅ ምን አስከተለ?

4. አዲስ ንጉስ በግብፅ ነገሰ። ይህም ፈርኦን ዮሴፍን አያውቅም ነበር (ቁጥር 18-19 አንብቡ)። ስለዚህ ሰው የተነገረን ነገር ምንድን?

**መልመጃ ፡ ከቁጥር 20-29 አንብቡ**

1. በቁጥር 20 ላይ የተጠቀሰው ዋና ባህሪ ማን ነው?
2. የዚህ ሰው የልጅነት ህይወቱ ምን ይመስላል (ቁጥር 20-21 አንብቡ)?
3. በቁጥር 23-25 የተጠቀሰው የሙሴ የተሳሳተ ግምት ምን ነበር? ለምንስ ከግብጽ ሸሸ (ቁጥር 26-28 አንብቡ)?
4. በቁጥር 29 ሙሴ ወደ ምድያም ምድር ከሸሸ በኃላ በምን ሞያ ተሰማራ ወይም ምን መስራት ጀመረ?

**ክፍል ሦስት**

**ከክፍል ሁለት የቀጠሉ የመልመጃ ጥያቄዎች**

**ከቁጥር 30-37 አንብቡ**

1. ከአርባ አመት በኃላ ሙሴ በምድረ በዳ በጎችን ሲጠብቅ ምን ተከሰተ (ቁጥር 30ን አንብቡ)?

____________________________________________________________

________________________________________________________

2. በቁጥር 34 መሰረት እግዚአብሔር የህዝብን ጭቆና ከተመለከተ ጩኸታቸውንም ከሰማ በኋላ ምን ለማድረግ አሰበ?

__________________________________________________________

____________________________________________________________

___________________________________________________________

3. እግዚአብሔር ሙሴ ምን እንዲያደርግ ፈለገ ?

____________________________________________________________

________________________________________________________

4. ሙሴ የእስራኤላዊያን_______________________እና ________________________ በሚነደው ቁጥቆጦ በተገለጠው በ_______________________ መላእክ ተላከ (ቁጥር 35ን አንብቡ)፡፡
5. በቁጥር 36 መሰረት ሙሴ ህዝቡን አውጥቶ__________________________________________________እና ___________________________________________________አደረገ፡፡
6. ቁጥር 37 እንደሚነግረን ሙሴ ለህዝቡ እግዚአብሔር ከ__________________________________________________እንደ እኔ ያለ __________________________________________________ያስነሳል አላቸው፡፡

**መልመጃ**

**ከቁጥር 38-43 አንብቡ**

1. ቁጥር 39-42 እንደሚነግረን ምንም እንኳን ሙሴ "ህያውን ቃል" ቢነግራቸውም አባቶቻቸው ምን አይነት መልሶችን ሰጡ? ሃሳባቸውስ የት ነበር?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

___________________________________________________________

ቁጥር 40-41 ስለ አምላካቸው ምን ይጠቁመናል?

________________________________________________________

2. በቁጥር 42 መሰረት እግዚአብሔር ምን አደረገ?

_______________________________________________________

3. እግዚአብሔር ህዝቡ ወደ___________________________________እንዲሄድ አደረገ (ቁጥር 43 አንብቡ)፡፡

**መልመጃ፡** ቁጥር 44-55 አንብቡ

1. ይህ ክፍል እስራኤላዊያን በ________________________ መሪነት ከምድረ በዳ ጀምሮ ይዘውት ስለመጡት ________________________ ይናገራል።
2. በቁጥር 46 ላይ ዳዊት እግዚአብሔርን የጠየቀው ነገር ምንድን ነው?

   ________________________
3. በቁጥር 47 መሰረት የእግዚአብሔርን መቅደስ የገነባው ማን ነው?

   ________________________

**ማስታወሻ፡**

የእሲጢፋኖስ መልእክት እንደሚነገረን አይሁዳዊያን ራሳቸውን ከቦታና ከመቅደስ ጋር ያቆራኙሉ። ቦታውንና መቅደሱን የሰጣቸውን አምላክ መታመን ግን ያቅታቸዋል። እግዚአብሔር ግን ከመቅደሱም፤ ከህጉም፤ ከቦታም በላይ ታላቅ ነው። ሊታመንም ይገባዋል። ለዚህም ነው እስጢፋኖስ ንስሀ እንዲገቡ የነገራቸው። እየሱስም እንደተናገረው እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በእውነትና በመንፈስ ያመልኩታል።

**መልመጃ፡** ቁጥር 51-53 አንብቡ

1. በቁጥር 51-53 ላይ እስጢፋኖስ ስለ ከሳሾቹ ምን ተናገረ?

   ________________________

   ________________________

   ________________________
2. ህጉን እንደሚጠብቁ ይናገራሉ። ህጉ ለእነርሱ ቅዱስ ነው። ነገር ግን ቁጥር 53 ስለ እነዚህ ሰዎች ምን ይላል?

   ________________________

   ________________________

**የቤት ስራ፡** ሐዋ 7፡ 54-8፡1 አንብቡ

**መልመጃ፡**

1. ለእስጢፋኖስ ንግግር ሊቀ ካህኑና እንዲሁም ሌሎች ሰዎች የሰጡት መልስ ምንን ነው (ቁጥር 54 አንብቡ)?

   ________________________

   ________________________
2. በቁጥር 55 እና 56 መሰረት የእስጢፋኖስ ንግግር ምን ላይ ያተኮረ ነበር?

3. ቁጥር 57-58 ምን ይነግረናል

4. የኢየሲስ መስቀል እስጢፋኖስ ተመልክቶ ይሆን አይሁን አይታወቅም። ነገር ግን እስጢፋኖስ ሲወገር ምን ተናገረ (ቁጥር 59-60 አንብቡ)?

5. እየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ የተናገረውን አስታውሱ። መዝ 31፡5ንም አንብቡ።

**ክፍል አራት፡**

**የማሰላሰያ ነጥቦች**

1. እስጢፋኖስ የመጀመሪያው ሰማእት ሆነ። ይህ ሰው በእግዚአብሔር ሀይልና መንፈስ የተሞላ ሰው ነበር። የተቃወሙት ሁሉ እርሱ የሚናገርበትን መንፈስ እና ጥበብ ሊቋቋሙ አልተቻላቸውም ነበር። ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ሀይልና መንፈስ ከእርሱ ጋር ቢሆንም እስጢፋኖስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰቀሉትና ባሰቃዩት ሰዎች ተወግሮ ሞተ። ይህን ታሪክ አሰላስሉ

2. በዚህ ታሪክ መሰረት በምኩራብ ሰዎች፤ በህግ አስተማሪዎች፤ በሽማግሌዎች እና በእስጢፋኖስ መካከል የነበረውን ጦርነት ወይም አለመስማማት እንዴት ትገልጸዋለህ በሐዋ 7፡51 መሰረት ዋናው ጉዳይ ምን ነበር?

በሐዋ 7፡55 መሰረት እስጢፋኖስ ወደ ሰማይ ሲመለከት ምን አየ?

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ህይወት ህያው የሆነውን ኢየሱስን መመልከት ይችላል። መንፈስ ቅዱስን የሚቋቋም ህይወት ግን ሙት መንፈስ ነው። ምክንያቱም 2 ቆሮ 3፡6

__________________________________ይነግረናል፡፡ ዮሐንስ 6፡ 63-65 አንብብ፡፡ ቁጥር 63 በሚገባ ፃፉ

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ወደ ህይወት የማዛመድ ነጥቦች፡**

1. ሰዎች አንገተ ደንዳና እና ያልተገረዘ/ ያልተገራ ልብ እና ጆሮ ያለው/ያለት ይልኛል፡፡ መንፈስ ቅዱስን የምትቋቋም / የሚቋቋም ይሉኛል ወይስ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መንፈስ ቅዱስ በመራው መንገድ የሚሔድ/የምትሔድ ታዛዥ ይሉኛል ?

____________________________________________________________________

______________________________________________________________________

__________________________________________________________________

2. መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ጌታና አዳኝ እንደሆነ እንዳምን አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን ሰዎች ምስክርነቱን ቢያጥላሉትም በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ለሰዎች የምመሰክረው መቼ ነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

________________________________________________________________

**መግቢያ፡** በሐዋ 8 ላይ በእየሩሳሌም ታላቅ______________________________ በ ____________________________ ላይ መነሳቱን እናነባለን፡፡ ከዚህም የተነሳ አማኞች በየ ________________________እና______________________________ተበተኑ፡፡

ኢየሱስ በሐዋ 1፡8 የተናገረውን አስታውሱ፡፡

የእርሱ ምስክርነትና ተጽእኖ ከእየሩሳሌም ወጥቶ በየከተማው እየተስፋፋ መጥቷል፡፡ ሐዋ 8፡4 ስለ ተበተኑት ደቀ መዛሙርት ምን ይነግረናል

______________________________________________________________________

እነዚህ ሰዎች በሔዱበት ሁሉ የሚናገሩት ነገር አለ፡፡ በሔዱበት ሁሉ ይህንን ታሪክ ይናገራሉ፡፡ በዚህ ጥናት ፊሊጶስ የሚባል ሰው እንተዋወቃለን፡፡ ይህ ሰው ከአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መሐል

አይደለም። ነገር ግን ሐዋ 6፡5 እንደሚነግረን ከሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት አንዱ ነበር። በተጨማሪም ሐዋ 6፡1 እንደሚነግረን ይህ ሰው በማእድ አገልግሎትም ያሉ ባልቴቶችን ያገለግላል።

በ ሐዋ 6፡3 መሰረት

__________________________________________________________

__________________________________________________________

**የቤት ስራ፡ ሐዋ 8፡ 4-8ን አንብቡ**

**መልመጃ፡**

1. ________________________________________ከተበተኑት ሰዎች አንዱ ነበር። በ____________________________________ወደ ሚገኝ ከተማም ሄደ። መጽሐፍ ቅዱሳችሁ የከተማ ጠቋሚ ካርታ ካለው ፊልጶስ የሄደበትን ከተማ ጠቁሙ። እንደምትመለከቱት ሰማሪያ በሰሜን በሚገኘው ገሊላ እና በደቡብ በሚገኘው ይሁዳ መካከል ይገኛል። ፊልጶስ የሄደባት በሰማሪያ የምትገኝ ከተማ አልተፃፈልንም። ነገር ግን ኢየሱስ በሐዋ 1፡8 የተናገረውን አስታውሱ። ወንጌል ተናጋሪዎች ከእየሩሳሌም ወደ ሰማሪያ እንዲሄዱ የተናገረው ቃል በዚህ ስደት ተፈጸመ።
2. ፊሊጶስ በሰማሪያ ምን አደረገ ?(ቁጥር 5ን አንብቡ)።

   __________________________________________________________

   ____________________________________________________

   በፊሊጶስ በሄደበት ከተማ ወንጌልን መስበክ ጀመረ። ይህ ክፍል እንደሚነግረን እየሱስ መሲህ እንደሆነ በከተማው ማወጅ ጀመረ።
3. ህዝቡ ለፊሊጶስ መልእክት ምን ምላሽ ሰጠ ?(ቁጥር 6ን አንብቡ)።

   __________________________________________________________

   __________________________________________________________

   ___________________________________________________

4. በዚህ ክፍል መሰረት የተከናወኑትን ሁለት ተአምራት ጥቀስ

   ሀ.________________________________________________________

   _______________________________________________________

   ለ.________________________________________________________

   _______________________________________________________

5. ለሰሙት ቃልና ለተመለከቱት ተአምራት ህዝቡ የሰጠው መልስ ምንድን ነው ?(ቁጥር 8ን አንብቡ)፡፡____________________________________________

____________________________________________

**ክፍል አምስት**

**ትምህርት**

ሐዋ 8፡9-13 ስምኦን ስለ ሚባል ሰው ይተርክልናል፡፡ ይህም ሰው ይጠነቁል ነበር፡፡ ህዝብም ይህ "ሰው ታላቁ ሀይል በመባል የሚታወቀው መለኮታዊ ኀይል ያለው ነው" በማለት ከልቡ ያዳምጡት ነበር፡፡ ህዝብም ስለሚሰራው ድንቅ ስራ ይከተለው ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ፊሊጶስ የእግዚአብሔርን መንግስት የምስራች እየሰበከ ስምኦን ወዳለበት ከተማ መጣ፡፡ ህዝቡም ወንጌልን ሰምተው አመኑ ተጠመቁም፡፡ ክፍሉ እንደሚነግረን ስምኦንም በተመለከተው ተአምራት ተገረመ ተደነቀ፡፡ አምኖም ተጠመቀ፡፡ የሚቀጥሉት ምእራፎች እንደሚነግሩን ስምኦን ፊሊጶስ ያደርግ እንደነበርው ሁሉ እጅ በመጫን ለሰዎች መንፈስ ቅዱስን መስጠትና ሰዎችን ማስደነቅ ፈለገ፡፡ ከዚህም ፍላጎቶ የተነሳ በገንዘቡ ይህን ችሎታ መግዛት ፈለገ፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስም ከእየሩሳሌም መጥተው ነበር፡፡ ስምኦን ገንዘብ ለመክፈል በፈለገ ጊዜ ጴጥሮስ የሰጠውን መልስ ከቁጥር 20-21 አንብቡና ዘርዝሩ፡፡

ሀ. በቁጥር 20 መሰረት መልሱ

____________________________________________

ለ. በቁጥር 21 መሰረት መልሱ

____________________________________________

ሀ. በቁጥር 22 መሰረት መልሱ

____________________________________________

ሀ. በቁጥር 23 መሰረት መልሱ

____________________________________________

የስምኦን መልስ በቁጥር 24 መሰረት ምን ነበር ?

____________________________________________

**የማሰላሰያ ነጥቦች**

1. ስምኦን ጠንቋይ የነበረ ሰው ነው፡፡ በዚህም ተግባሩ ትልቅ እውቅና ለራሱ ያከማች ነበር፡፡ ራሱንም ታላቅ ያደርግ ነበር፡፡ ህዝብም ይህ "ሰው ታላቁ ሀይል በመባል የሚታወቀው መለኮታዊ ኀይል ነው" በማለታቸው እጅግ ይደሰት እና ይኩራራ ነበር፡፡ ፊሊጶስ ወደዚያ ከተማ ሄዶ ወንጌልን በሀይል እስከሚሰብክበት ጊዜ ድረስ ስምኦን በሰላም ይኖር ነበር፡፡ የስምኦን ዋና ፍላጎት የተሻለ ተአምራት የሚያደርግበትን ሀይል በገንዘቡ ከነ ጴጥሮስ መግዛት ነበር፡፡

ጴጥሮስም የእግዚአብሔር ስጦታ በገንዘብ እንደማይገዛ ነገረው፡፡ የስምኦን ልብ በእግዚአብሔር ፊት ቅን አልነበረም፡፡ ስለዚህም ንስሀ እንዲገባ ነገረው፡፡

2. ስለ ጥንቆላ ምን ታውቃለህ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ እጅ ስለመጫን ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

4. ስምኦንስ እጅ በመጫን ስለአለው ጸጋ ያለው አመላከት ምን ይመስላል?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

5. አንድ ሰው በጥንቆላ ስራ ከተሞላ  በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ ለመሞላት ቦታ ይኖረዋል ብለህ/ሽ ታስቢያለሽ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

# ጥናት ስድስት

# ሂዱ!

## የሐዋሪያት ስራ ምእራፍ 8-9
## ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፤ ፊልጶስ እና ሳኦል

---

### ትምህርት ስድስት

*መግቢያ*

ትምህርት ስድስት: *ሐዋ* 8-9

- የፊልጶስ ወደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መላክ
- በመንገዱ ላይ
- የማስላሰያና ከህይወት ጋር የማዛመድ ነጥቦች
- የሐናንያ መላክ
- የሳኦል ተልእኮ

## መግቢያ

“ሂዱ” የምትለው ቃል ከሁለት ፊደል የተዋቀረች ብትሆንም በውስጧ ግን ትልቅ ትርጉም ይዛለች። ወደ አለም ሁሉ “ሂዱ”። ወይም “ሂዱ” ሰዎችን ደቀ መዛሙርት አድርጉ የሚሉ ትእዛዞች በዚህች ሁለት ፊደል ላይ የተንጠለጠሉ ቃላቶች ናቸው። ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ”አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ“ ብሏል። ስለዚህ ይህ ጌታ ዛሬም ልጆቹን ወደ ተለያየ ቦታ ይልካል። ሰላም ወዳለበት ሰላም ወደ ሌለበት ቦታዎች ሊልከን ይችላል።

ዛሬ ለእኛ የተሰጠን ተልእኮ ከኢየሱስ ተልእኮ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተልእኮ ነው። ኢየሱስ ሰዎችን ደቀ መዝሙር እንዲያደርግ፣ ሰዎችንም እንዲያገኝ (ለምሳሌ በሰማሪያ እና በእያሪኮ መንገድ ላይ ሰዎችን ተገናኘ) ተላከ። በዚህም ተልእኮው ሰዎችን ለድነት አበቃ። ወደ ድነት መራቸው።

ይህንን ጥናት ስታጠኑ ጌታ ለእናንተ ምን እየተናገረ እንደሆነ ልብ በሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ የሚናገራችሁን እረኛችሁን አድምጡ፤ “እኔን ላከኝ፤ እሰማሀለሁ በሉ።” ፊልጶስ ወደ ጃንደረባው ተላከ። የምስራቹንም አበሰረ። ጃንደረባውም የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ እየተደሰተ ሄደ። ሳኦልም ከተለወጠ በኋላ “ሂድ“ የሚለውን ተልዕኮ በሐናንያ በኩል ተቀበለ።

እናንተም በዚህ ጥናት እረኛችሁ ኢየሱስ ”አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኃለሁ“ ሲል እነሆ አድምጡ።

## ትምህርት ስድስት

**ክፍል አንድ ፡**

**የቤት ስራ፡** የሐዋ 8፡ 26-40 አንብቡ፡፡

**መልመጃ**

13. በቁጥር 26 መሰረት የፊልጶስ ተልእኮ ምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

14. ከላይ በተመለትነው ቁጥር ላይ ፊልጶስ መልእክት ተነገረው፡፡ የጌታም መላእክ እንዲሄድ ነገረው፡፡ ስለዚህም ሄደ፡፡ ፊልጶስ ታዛዥ ሰው ነበር፡፡ ከእየሩሳሌም እስከ ጋዛ ያለው መንገድ በግምት 80 ኪሎ ሜትር ይሆናል፡፡ በቁጥር 27 መሰረት ፊልጶስ ማንን አገኘ?

______________________________________________

______________________________________________

የመምረጥ ሀላፊነት ለደቀ መዛሙርቱ ተሰጣቸው፡፡

15. ይህ ሰው ማን እንደሆነ ክፍሉ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ይህ ሰው የት ነበር

______________________________________________

ፊልጶስ ይህንን ሰው ምን እየሰራ አገኘው?

______________________________________________

______________________________________________

ይህ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር፡፡

16. መንፈስ ለፊልጶስ ምን ነገረው (ቁጥር 29ን አንብቡ)?

______________________________________________

______________________________________________

17. በመቀጠል ፊልጶስ ምን አደረገ ?

______________________________________________

______________________________________________

18. (ቁጥር 30ን አንብቡ) ፊልጶስ ሰውዬውን ምን ጠየቀው?

______________________________________________________________________

__________________________________________________________________

19. ኢትዮጲያዊው ጃንደረባስ ምን መለሰ?

______________________________________________________________________

__________________________________________________________________

20. ኢትዮጲያዊው ጃንደረባ ፊልጶስ ወደ ሰረገላው እንዲወጣ ጠየቀው፡፡ ይህ ሰው ምን እያነበበ ነበር የሚያነበውንስ የት አገኘው?

______________________________________________________________________

__________________________________________________________________

21. ፊልጶስን ምን ጠየቀው?

____________________________________________________________________

22. በቁጥር 35 መሰረት ፊልጶስ ሰውዬውን ያስተማረው ከየትኛው መጽሐፍ ነው? ምንስ አስተማረው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

__________________________________________________

23. በቁጥር 37 መሰረት እነዚህ ሰዎች __________________ጋር ሲደርሱ ጃንደረባው ፊልጶስን ምን ጠየቀው?

____________________________________________________________________

24. በቁጥር 38 መሰረት ፊልጶስ ምን አደረገ?

____________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________

25. ቁጥር 39 ስለ ፊልጶስ ምን ይነግረናል?

____________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_______________________________________________________________

26. ኢትዮጲያውዊ ጃንደረባ ወዴት ሄደ?____________________________________ በቁጥር ስምንት መሰረት የፊልጶስ አገልግሎት ምን ለውጥ እንዳመጣ አስታውስ፡፡ ታላቅም _____________________________________ ሆነ፡፡

በመቀጠል ፊልጶስ ወደ አዛጦን ወረደ፡፡ በቁጥር 40 መሰረት በመንገድ ሲያልፍ ምን አደረገ?

_______________________________________________

_______________________________________________

27. በተጨማሪም በሐዋ 21፡ 8-9 ስለ ፊልጶስ ምን እንማራለን?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

**የማሰላሰያ ነጥብ**

ፊልጶስ ተልእኮውን የፈጸመ ሰው ነው፡፡ ወንጌልን ሰበከ፡፡ በእርግጥ በቁጥር 47 መሰረት ፊልጶስ የታዘዘው ከእየሩሳሌም ወደ ጋዛ በሚያወርደው በምድረ በዳ መንገድ እንዲሄድ ነው፡፡ የታዘዘውንም አደረገ፡፡ በመንገዱም ላይ ሲሔድ ሰው አገኘ፡፡ አንድ አፍታ ጌታ በህይወት መንገዳችሁ ላይ እንድታናውኑ የሰጣችሁን ስራዎች አስቡ፡፡ እነዚህን ስራዎች እየሰራችሁ ይሆን?

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች**

1. ህይወታችሁን የምትኖሩት በእግዚአብሔር እንደታዘዘ ሰው ወይም ተልእኮ እንዳለበት ሰው በየእለቱ የሚያጋጥማችሁን እድል የእግዚአብሔርን ፍቅር ላላወቁ ሰዎችስ ወንጌልን ለመንገር ምን ያህል ትጠቀሙበታላችሁ?_______________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. አንድ ሰው በቀን ውስጥ ብዙ ስራዎችን ይሰራል፡፡ በቤት ውስጥ፣በመንገድ ላይ፣ በመስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰሩ ብዙ ስራዎች አሉ፡፡ በእነዚህ ስራዎች መካከል ወንጌልን ያልሰሙ ሰዎች ወደ እኛ ይመጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ወንጌልን እንነግራቸዋለን ወይስ አጥምዶ የያዛችሁ ስራችሁ ላይ ብቻ ትጠመዳላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

**ክፍል ሁለት**

**የማሰላሰያ ነጥብ**

ምንም እንኳን በመንገድ ላይ ቢሆንም ፊልጶስ ለኢትዮጲያዊው ጃንደረባ እንደተላከ ገብቶት ነበር፡፡ ወደ ሰረገላው ሲሄድም ጃንደረባው ትንቢተ ኢሳያስ 53ን እያነበበ አገኘው፡፡

ፊልጶስም እንዲህ የሚል ጥያቄ ጠየቀው "የምታነበውን ታስተውላለህ/ትረዳለህ?" በእርግጥ ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ከክርስቶስ ጋር ለማገናኘት ጓግቶ ነበር፡፡

## ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች

4. በህሊናህ/ሽ ፊልጶስ ኢሳ 53ን ከየምስራቹ ወንጌል ጋር በማገናኘት የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከኢየሱስ ጋር ለማገናኘት እንዴት እንደጓጓ ያሳያል፡፡ እናንተ ዛሬ የምስራቹን ድምጽ ለሰዎች ለማሰማት ምን ያህል ትጓጓላችሁ? በምድር ላይ ካለ ከየትኛውም ዜና የሚበልጠውን ይህንን ዜና በቅርቡ ለማን መንገርና እንዴት መንገር እንደምትችሉ አብሯችሁ ይህንን ጥናት ከሚያጠና ሰው ጋር ተነጋገሩ?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

_____________________________________________________

5. ፊልጶስ "የምታነበውን ታስተውላለህ/ትረዳለህ?" የሚል እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ ጥያቄ ጠየቀ፡፡ እናንተስ ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ እያነበቡ ነገር ግን ጌታ እየሱስን የማያውቁትን ሰዎች "የምታነበውን ታስተውላለህ/ትረዳለህ?" ብላችሁ ትጠይቃላችሁ?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

ጌታ ይህንን ጥያቄ ለሰዎች እንድናቀርብ ይርዳን፡፡

**የማሰላሰያ ነጥብ**

ቁጥር 35 እንደሚነገረን ፊልጶስ ጃንደረባው እያነበበ የነበረውን መጽሐፍ ተጠቅሞ የኢያሱስን ወንጌል በሚገባ ነገረው፡፡ ፊልጶስ ጃንደረባው ከነበረበት ቀጠለ፡፡ ማለትም በማንበብ ላይ የነበረውን መጽሐፍ አብራራለት እንጂ ከአዲስ ነገር አልጀመረም፡፡ ስለዚህ ወንጌል ስንመሰክር ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ወይም የሚያውቁትን ነገር ለመረዳት መሞከር ስኬታማ ሊያደርገን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ፊሊጶስ ጃንደረባውን ለመረዳት የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቅ ነበር፡፡ እኛም ወንጌልን ለማዳረስ ስለ ምንመሰርለት ሰው ጥሩ መረጃ ቢኖረን ውጤታማ እንሆናለን፡፡

## ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ጸጋ ይደግፋል፡፡ ጸጋው የደነደኑ ልቦች እንዲከፈቱ ያደርጋል፡፡ ጸጋው ጥላቻን፣ ምሬትን፣ ጥርጣሬን፣ ግጭትን እንድናልፍ ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ በምን አይነት ሁኔታ ለማን እንዲደርስ ትፈልጊያለሽ/ትፈልጋለሁ?

2. ዛሬ ማንን ወይም እነማንን ባሉበት ሁኔታ ልወዳቸውና ፍቅርን ላስተላልፍላቸው ይገባል?

### የማሰላሰያ ነጥብ

ወደ ታሪኩ መጨረሻ ስንደርስ እንደምንረዳው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ደስ እያለው መንገዱን ቀጠለ። መቼስ ደስተኛ የሆነ ሰው ደስታውን ለሰዎች ሊያካፍል እንደሚችል ግልጽ ነው። ስለዚህ ይህ ሰው ወንጌል እንዲስፋፋ ምክንያት መሆን ይችላል። እኛስ ዛሬ ለወንጌል መስፋፋት ምክንያቶች ነን?

### ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄ

በመቀጠልነስለ ስሜት ጥቂት እንነጋገር። ስለ ደስታ ያላችሁ አመለካከት ምን ይመስላል?

ቀኖችህንስ የማሳልፈው በደስታ ነው?

የሚከተለውን ጸሎት አብረን እንጸልይ። ጌታ ሆይ ልቤን በደስታና በምስጋና እድትሞላው እጸልያለሁ።

## ክፍል ሦስት

### መግቢያ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከተዘገቡልን በጣም ከሚገርሙ ታሪኮች አንዱ የሳኦል ታሪክ ነው። ስለ ዚህ ሰው መተረክ የተጀመረው በሐዋ 7 ላይ ነው። ቁጥር 58 እንደሚነግረን፤ እስጢፋኖስን የወገሩት ሰዎች ልብሳቸውን ያስቀመጡት ______________________በተባለ ሰው እግር ስር ነው። እስጢፋኖስ ሲወገርም የአይን ምስክር ነበር። ሐዋ 8፡1 እንደሚነገረን ሳኦል______________________ነበር። በመቀጠል በሐዋ 8፡1 እና 3 በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለተነሳው ትልቅ ስደት እንማራለን። ስደቱ ምን ይመስል ነበር? አብራሩ

በሚቀጥሉት ምእራፎች ውስጥ ስለ ሳኦል ብዙም አልተነገረንም። የሐዋሪያት ስራ ምእራፍ 9 ግን ስለ ሳኦል መተረክ ይጀምራል።

**የቤት ስራ፡** ሐዋ 9፡ 1-19 አንብቡ። በተጨማሪም ሐዋ 22፡ 3-16 እና 26፡9-18 አንብቡ።

**መልመጃ፡**

1. ሳኦል አስቦበት እና አቅዶበት የጌታን ደቀ መዛሙርት ያሳድድ ነበር። ቁጥር 1 ስለዚህ ሰው ምን ይነግረናል?
2. በቁጥር 2 መሰረት ከ ሊቀ ካህኑ ምን አግኝቶ ነበር? ምንስ ?
3. ሳኦል በደማስቆ መንገድ ላይ ምን ገጠመው (ቁጥር 3)?
4. ሳኦል ምን የሚል ድምጽ ሰማ?
5. በቁጥር 5 መሰረት የሳኦል ምላሽ ምን ነበር? ለጠየቀው ጥያቄስ ያገኘው መልስ ምን ነበር?
6. በቁጥር 6 መሰረት ምን እንዲያደርግ ነው የታዘዘው?
7. ከሳኦል ጋር አብረው ሲጓዙ የነበሩ ሰዎች ላዩት ነገር ምን ተሰማቸው (ቁጠር 7ን አንብቡ) ?
8. ሳኦል ከወደቀበት ሲነሳ ምን አይነት ሁኔታ ላይ ነበር (ቁጠር 8ን አንብቡ)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

9. አብረውት የነበሩ ሰዎች እጁን ይዘው ወዴት ወሰዱት?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

10. ስለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ቁጥር 9 ምን ይነግረናል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

11. ቁጥር 10 ሐናንያ የሚባል ደቀ መዝሙር ያስተዋውቀናል፡፡ ለዚህ ሰው ጌታ በህልም ተገልጦለት ነበር፡፡ ሐናንያ ወዴት ተላከ (ቁጠር 11ን አንብቡ)፡፡ ማንንስ ይፈልግ ነበር፤ በዚያስ ምን ሰራ?________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

12. ቁጥር 13-14 መሰረት ሐናንያ ምን ማድረግ ሲከብደው እንመለከታለን?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

13. ጌታም ሐናንያ የተነገረው ቦታ እንዲሔድ የበለጠ ተጫነው፡፡ ጌታስ ለሐናንያ ስለ ሳኦል ምን ነገረው (ቁጠር 15-16 አንብቡ)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

14. ሐናንያ በመታዘዝ ወደ ሳኦል ሄደ፡፡ ቁጥር 17 እንደሚነግረን እጁንም ጫነበት

ሀ. ሐናንያ ማን ላከኝ አለ?

____________________________________________________________

ለ. ለምንስ ተላከ?

1.__________________________________________________________

____________________________________________________________

2.__________________________________________________________

____________________________________________________________

15. ቁጥር 18-19 ምን አዳዲስ ነገሮች ሆኑ?

ሀ.____________________________________________________________

ለ.____________________________________________________________

ሐ.____________________________________________________________

**የማሰላሰያ ነጥብ፡**

1. የሳኦልን መለወጥ ስታስብ ወደ አእምሮህ የሚመጡልህ ነገሮች ምንድን ናቸው
2. እንደ ሳኦል በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የሚያምፅና ልቡ የደነደነ ሰው ይለወጣል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ነገር ግን ይህ ለእግዚአብሔር እንደሚቻል ይህ ክፍል በሚገባ ያስረዳናል። ሳኦል የጌታን ስም የሚጠሩትን ሁሉ ለማሳሰር ከሊቀ ካህኑ የተጻፈለትን ደብዳቤ በእጁ ይዞ ነበር። አማኞችን ለመግደልና ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ወደ ኋላ አይልም ነበር። ምንም እንኳን እነዚህን ጉዳዮች ለማስፈፀም ልቡ የጨከነ ሰው ቢሆንም ጌታ በሚደንቅ ሁኔታ ተገናኘው። “ሳኦል ሳኦል ስለ ምን ታሳድደኛለህ” የሚል ድምጽ ሰማ። ሳኦል አማኞችንና ቤተ ክርስቲያንን በማሳደዱ ሳያውቀው እያሳደደ የነበረው የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስን ነበር። ጌታም ለምን ታሳድደኛለህ አለው።

3. ከጥያቄውም በኋላ ከወደቀበት እንዲነሳ ብሎም ወደ ደማስቆ እንዲሔድ ታዘዘ። አይኖቹም ታውረው ስለነበር በሰዎች ምሪት መጓዝ ግድ ሆነበት። ራሱም ሙሉ ለሙሉ ሰዎች ላይ መጣል ነበረነት። የሚመካበት አይንም ሆነ የባለ ስልጣናት ደብዳቤ በእጁ የለም። ሀይለኛና አስፈሪ የነበረ ሰው ከመቅፅበት ማየት የማይችልና ሰዎች እጁን ይዘው የሚመሩት ሰው ሆነ። የሚሄድበትን መንገድም የሚመርጡለት ሰዎች ሆኑ። ይገርማል። ይህም ወደ ሚሔድበት ቦታ ሁሉ በትህትና እንዲሔድ ይረዳዋል። እናንተስ የሰዎች እርዳታ አስፈልጓችሁ ያውቃል? እርዳታ መፈለጋችሁ ትህትና ጨመረላችሁ ወይስ ትምክህተኛ አደረጋችሁ?

   ____________________________________________________________

   _______________________________________________________

4. በደማስቆ የሚኖር የጌታ ተከታይ የነበረ ሐናንያ የሚባል ሰው ነበር። ይህም ሰው ጌታ በራእይ ወደ እርሱ ከመምጣቱ በፊት የራሱን ስራ ይሰራ የነበረ ሰው ነበር። ልብ ብላችሁ ካያችሁ በዚህም ታሪክ በድጋሚ “ሂድ” የምትለውን ትእዛዝ ማጤን ትችላላችሁ፡ሐናንያ ወደ ሳኦል ተላከ። ሐናንያ ይህንን ትእዛዝ ለመቀበል ከብዶት ነበር። ምክንያቱም የተላከው ሰዎችን ለማሰር ስልጣል ወደ ነበረው ሳኦል ወደ ተባለ ሰው ነበርና ነው። እግዚአብሔርም ሳኦል ወንጌልን ለአይሁድ እንዲህም ለአህዛብ ለማዳረስ የተመረጠ ሰው እንደሆነ ለሐናንያ ነገረው።ምንም እንኳን ይህ ትእዛዝ ከባድ ቢሆንም ሐናንያ በመጨረሻ ታዘዘ። ሔደም። ሳኦልም አይኖቹ እንዲያዩ በመንፈስ ቅዱስም እንዲሞላ ጸለየ።

**ከህይወት ጋር የማዛመድ ጥያቄ**

1. መንፈሳዊ አይኖችህ ታውረው የኢየሱስ ስምን የሚጠሩትን አሳደህ ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ ወይም የሚያሳድዱ ሰዎችን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ እነዚህ ሰዎች እያሳደዱ ያሉት እየሱስን ነው። ጌታን እያሳደዱ እንደሆነ ልተነግሯቸው ትችላላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

2. ጌታ አይናቸው የተጋረደ እናም ሊከፈትላቸው የሚገባ ሰዎችን ወደ ሕይወታችሁ እንዲያመጣ እናንተም ወደ እውነት መምራት እንድትችሉ ጸልዩ።
3. ሐናንያ ወደ ሳኦል የተላከበት አንዱ አላማ ሳኦል በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ነው። የጌታም መንፈስ ቃሉ በሚነበብበት ጊዜ እና በሚሰማበት ጊዜ ወደ ሐናንያ መጣ። እናንተንም ዛሬ የጌታ መንፈስ ይሙላ። የጌታ መንፈስ ዛሬም በሰዎች አማካኝነት እንዲሁም በቃሉ በኩል ወደ እናንተ ይምጣ።_______________________

**ክፍል አራት፡**

**በጥልቀት መቆፈር፡** ወደ ቀጣዩ ጥያቄ ከመሔዳችሁ በፊት 2 ቆሮ 11፡ 21-29 አንብቡ።

1. ቁጥር 22-23፡ ይህ ክፍል ጳውሎስ የተባለው ሳኦል ማን እንደሆነ ምን ምን ይነግረናል?

   ሀ.___________________________________________

   ለ.___________________________________________

   ሐ.___________________________________________

   መ. ___________________________________________

2. ቁጥር 23-25 አንብቡ፤ ይህ ክፍል ጳውሎስ ስለ ወንጌል ሲል ምን ምን እንደተሸከመ ይነግረናል?

ሀ.___________________________________________

ለ.___________________________________________

ሐ.___________________________________________

መ. ___________________________________________

ሠ.___________________________________________

ረ. ___________________________________________

3. በቁጥር 25-29 መሰረት ጳውሎስ ስለደረሰበት አደጋ እና ስቃይ አብራሩ።

   ___________________________________________

**የማሰላሰያ ነጥብ፡**

ጌታ በሐዋ 9፡16 ላይ ለሐናንያ ጳውሎስ ስለ ወንጌል ሲል ብዙ መከራ እንደሚቀበል ነግሮታል። በሁለተኛ ቆሮንቶስ ምእራፍ አስራ አንድ ጳውሎስ ስለ ደረሰበት አንዳንድ መከራዎች እናነባለን። ጳውሎስ ከደረሰበት መከራ የተነሳ ፊቱን ከጌታ ላይ አላነሳም። ይልቅስ ስለ ደረሰበት መከራ፣ስደት፣ ለስጋውም ስለ ተሰጠው መጎሸሚያ በ2ቆሮ 12፡7 ላይ ይናገራል። ጌታ በቁጥር 9 ላይ ስለ እርሱ የተናገረውን ጻፍ።

3. ጌታ ለተናገረው ነገር የጳውሎስ ምላሽ ምን ነበር?

4. ቁጥር 9ን በቃላችሁ ማነብነብ እንድትለምዱ እመክራችኋለሁ። ጳውሎስ እንደ ተናገረው በደረሰብን መከራ ምክንያት የደከምን ስንመስል እኛ ግን ብርቱዎች ነን።

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ አንዳንዴ ልክ እንደ ጳውሎስ ከአንተ ሀሳብና እቅድ ጋር እጋጫለሁ። የአንተን ሀሳብ በተቃወምኩበት ነገር ሁሉ ላይ ምህረትን አብዛልኝ። ደንዳንናውን ልቤን ሰብረህ ወደ ፈቃድህ አምጣኝ። በፍቅር ወደ ተዘረጉት የአንተ እጆች እንድመለስ እርዳኝ። አጥብቀህ ያዘኝ። መንፈስህ በውስጤ እምነትን ፈጥሯል። በዚህ እምነት አጽናኝ። ይህንን እምነት ከአንተ የተጋራሁትንም ፍቅር ለሰዎች በፈቃዴ እናም በደስታ እንዳጋራ እርዳኝ።

***መዝጊያ***

ይህ ጥናት የሳኦልን መለወጥ አሳይቶናል። እግዚአብሔርም የእርሱን ስም እንዲሸከም የጌታንም ስም ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገስታት እንዲሁም ለእስራኤላዊያን እንዲያደርስ መርጦታል። አሁን የጥናት አንድ መደምደሚያ ላይ ደርሰናል። አሁን *"የእግዚአብሔር ፍቅር፤ ህይወታችን!"* ወደ ተሰኘው ሁለተኛው ጥናት እንለፍ።